# ሥራና መጽሐፍ ቅዱስ

ከምኒልክ አስፋው

ይህ ክፍል በቀጥታ የተወሰደው ምኒልክ አስፋው "ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች" በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ ነው

እያንዳንዱ ሕዝብ የሥራ ባህል አለው። አንዱ ሕዝብ ለሥራ የሚሰጠው ስፍራ ከሌላው ሕዝብ የተለየ ነው። ለአንዱ ሕዝብ ሁሉ ነገር የሚተመነው በሥራ ፍሬ ሲሆን፣ ለሌላው ሕዝብ ደግሞ "በአምላኩ ትሩፋት" ብቻ ነው። እርሱ ከፈቀደ ዕድገት አለ፤ እርሱ ካልፈቀደ ትርፉ ዘጥ ዘጥ ብቻ ነው። ሁሉም ግን ሥራን በጥቅሉ ሕይወትን የሚያዩበት የየራሳቸው "የዕይታ አንጻር" አላቸው። የዕይታ አንጻሩ አምላኬ የሚሉት፣ ወጌ የሚሉት፣ እምነቴ የሚሉት፣ ዕውቀቴ የሚሉት፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ሥራን በተመለከተ እነዚህ የዕይታ አንጻሮች ወሳኝ ናቸው። ከተሞክሮ እንደምንረዳው ሰው የሚሆነውን፣ የሚሆነው ከሚያምነው ነገር ወይም ከሚከተለው መርሕ የተነሣ ነው[1]። ይህ አባባል ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ ለመፈተሽ ወደ ኋላ መሄድና የጥንቱን ሕዝብ ታሪክ መመልከት ያስፈልጋል።

## 1. ሥራ በጥንት ሕዝቦች ዘንድ

ስለ ሥራ ምንነት ከመነጋገራችን በፊት የጥንት ሕዝቦች ሥራን በተመለከተ የነበራቸውን ባህል መቃኘት ወደ ፊት ለምናነሣቸው ነጥቦች መልካም መንደርደሪያ ይሆነናል። እዚህ ላይ ለመመልከት የምንፈልገው የጥንት ግሪካውያኑን፣ ምሥራቃውያኑንና አይሁዳውያኑን የሥራ ባህልና ለሥራም ያላቸውን ግምት ነው። ከዚያም ነገሩን ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ጋር በማያያዝ እኛ ራሳችን ለሥራ ያለን ግምት ምን ይመስላል የሚለውን እንመለከታለን።

### 1.1. ሥራ በጥንት ግሪካውያን ዘንድ

ለጥንት ግሪካውያን ሥራ ርግማን ነው። ሥራ የነጻ ሰዎችን ክብር የሚያዋርድ ተግባር ነው። እንዲያውም "ሥራ" የሚለው ቃል የተገኘው "ሐዘን" ከሚለው ዘር አንቀጽ ነው[2]። በተለይ የጕልበት ሥራ የሚታየው የሰው ልጆችን ክብር "አዋራጅ" ተደርጎ ነው። የግሪካውያኑን ሕይወት (ኀሊናቸውን፣ እርምጃቸውን፣ ዕይታቸውን) በእጅጉ የቀረጹት ፈላስፎቻቸው እንደሚናገሩት፣ የሕይወት ግቢ ዕረፍት ነው - መዝናናት ደስ መሰኘት። ሥራ ዕረፍትን ስለሚጋፋ ለነጻ ሰዎች የተገባ አይደለም። ምክንያቱም ሥራ ባሪያ ያደርጋል። ሄሶይድ የተባለ የግሪክ ገጣሚ ስለ ሥራ ሲናገር፣ ሥራ የመጣው ኤሪስ ከምትባል "የሁከት ወይም የጥል አምላክ" ነው ይላል። ሌሎች የግሪክ ፈላስፎች እንደሚሉት ደግሞ ሥራ የአማልክት ቍጣ ነው። ዜውስ የተባለ አምላክ የሰውን ልጅ

[1] Max Weber "ማንኛውም ሐሳብ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ አለው" ይላል፡፡ በእርግጥም ሰዎች የሚያስቡትና የሚያደርጉት ነገር ተያያዥነት አላቸው፡፡ አንዱ ሌላውን የመግራት ኀይል አለው፡፡ Gary L. Almy, *How Christian is Christian Counseling: The Dangerous Secular Influences That Keep Us from Caring for Soul* (Wheaton, Ill.: Crossway Books, 2000), 17-88.

[2] Andriano Tilgher, *Work: What It Has Meant to Men through the Ages*, Trans. Doroty C. Fisher (New York: Arno Press, 1930), 3-9.

ለመቅጣት ሲያስብ ሥራን ፈጠረ፡፡ ሥራ የአማልክት መቅጫ በትራቸው ነው[3]፡፡

ሥራ በጥንት ግሪካውያኑ ዘንድ እንደ ርግማንና ቀኁጣ ሊታይ የቻለው፣ አማልክቶቻቸው ለሥራ የሚሰጡት ስፍራ ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡ አማልክቱ ለደስታ እንጂ ለሥራ ደንታ የላቸውም፡፡ ለተድላና ለፍስሓ እንጂ ለሥራ ቁብ የላቸውም፡፡ በግሪኮቹ እምነት አማልክት ለሥራ የሚነሡት፣ መንበራቸውን የሚቀናቀን ባላጋራ ሲነሣ አልያም የሰዎችን ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ጉባኤ ሲጠራ ብቻ ነው፡፡ ሆሜር የተባለ ባለቅኔ የአማልክቱን ሕይወት እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡፡ "መኖሪያችሁ ከቶ የማይደፈር ነው፤ በዚያ ዐውሎ ነፋስ የለም፤ ነጐድጓድ ዝናብ የለም፤ በረዶ የለም፡፡ ሰማዩ ብሩኅ ነው፤ ጭጋግም የለበትም፡፡ ከብሩኅ ሰማይ በስተላይ ጸዳል ሰፏል፡፡ በዚያም ቡሩካኑ አማልክት ዘመናቸውን ሁሉ ደስ እያላቸው ይኖራሉ"፡፡ ከሆሜር ገለጻ እንደምንረዳው በአማልክቱ ዐምባ ደስታና ፍሥሓ እንጂ ሥራ የለም፡፡ እንዴት ደስ ብሏቸው እንደሚኖሩ እንጂ ስለ ሥራ ሲጨነቁ አናይም፡፡

በጥንት ግሪካውያን ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ስለ ደስታና ፍሥሓ እንጂ፣ ስለ ሥራና ሠራተኛነት እምብዛም ሲወሳ አይታይም፡፡ አርስጣጣሊስ እንደሚለው፣ የሕይወት ግብ ደስታ/ ፍሥሓ ነው፤ ይህን እውን የሚያደርግልን ደግሞ ዕረፍት ነው፡፡ በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ "አምላክን መምሰል" ማለት ከሥራ ነጻ መሆን ማለት ነው[4]፡፡ ሥራ የባሮች ተግባር/ ሸክም በመሆኑ ነጻ ሰዎችን የሚያሳስብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ነጻ ሰዎች እንዲያስቡ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲጠበቡ፣ እንዲፈላሰፉ፣ እንዲያስተዳድሩ እንጂ እንዲሠሩ፣ እንዲጥሩ፣ እንዲደክሙ አልተፈጠሩም[5]፡፡

## 1.2. ሥራ በጥንት ምሥራቃውያን ዘንድ

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሥራ ባህል ልቆ ወይም ወድቆ የምናገኘው፣ ኅብረተሰቡ ከሚያመልከው አምላክ አልያም ከሚከተለው እምነት የተነሣ ነው፡፡ ኅብረተሰቡ የሚያመልከው አምላክ ታታሪ ሠራተኛ ከሆነ፣ ሕዝቡም ታታሪ ሠራተኛ ይሆናል፡፡ ኅብረተሰቡ የሚከተለው እምነት ትጉነትን የሚያበረታታ ከሆነ፣ ሕዝቡም ትጉ ይሆናል፡፡ ለዚህ አባባል ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የቡድሃ ሃይማኖት ነው፡፡ የቡድሃውያን ሕይወት የተቀረጸው በቡድሃ አምሳል ነው፡፡ የቡድሃን ምስል/ቅርፅ አይተነው እንደሆን፣ አንድ ፈረጠም ያለና ያለ ሥራ የተቀመጠ "አምላክ" ይታያል፡፡ ዐይኖቹ ተከድነዋል፤ እጆቹ ዘና ብለው ተቀምጠዋል፤ እግሮቹም ፈልሰስ ብለው ተዘርግተዋል፡፡ ብቻ አምላክየው ተደላድሎ ተቀምጧል፡፡ ግቡና ሐሳቡ ተግቶ መሥራት ሳይሆን ተኝቶ መቀለብ ነው[6]፡፡ እንዲያውም በቡድሃ እምነት ውስጥ "ሥራ" ለሚባለው ነገር ወይም ቃል (መጠሪያ) የለም፡፡ ሥራም እንደ አንድ አርእስት ተወስዶ ትምህርት አይሰጥበትም[7]፡፡

---

[3] Leland Ryken, *Redeeming the Time: A Christian approach to work and leisure* (Grand Rapids: Baker Books, 1995) ገጽ 71-85፡፡ የጥንት ግሪካውያኑና አይሁዳውያኑ ስለ ሥራ የተናገሩት ነገር በአብዛኛው የተወሰደው ከ Andriano Tilgher እና ከ Leland Ryken መጻሕፍት ነው፡፡

[4] Leland Ryken, *Redeeming the Time*, 71-73.

[5] ዝኒ ከማሁ ፤ ገጽ 159 ፡፡

[6] Thomas Schirrmancher, *God Wants You to Learn, Labour and Love* (Hamburg: Reformation Books, 1999), 16.

[7] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 16፡፡

## 1.3. *ሥራ በጥንት አይሁዳውያን ዘንድ*

*ከያህዌ የተነሣ የጥንት አይሁዳውያን ለሥራ ያላቸው ልብ ከማንም የተሻለ ነው። ይሁንና ከአካባቢያቸው ተጽእኖ የተነሣ ለሥራና ለሠራተኛነት ያላቸው አስተያየት፣ እውነተኛውን መነሻ እየሳተ መጣ። ሥራን ለባሮችና ለምርጦች እያለ ደረጃ የሚያበጅለት የግሪካውያኑ ፍልስፍና እነርሱንም ወረራቸው። ግሪኮቹ ማሰላሰሉ (የአእምሮ ሥራ ይሉታል) ለምርጦቹ፣ ተግቶ መሥራቱ (የጕልበት ሥራ ይሉታል) ለባሮቹ የተመደበ በመሆኑ፣ ሁላችንም በዕጣ ክፍላችን እንቁም በማለት የሚያስተምሩት ነገር፣ ውሎ ሲያድር "መንፈሳዊና ሥጋዊ ሥራ" የሚሉ ስሞች ወጡ ለት። ይህ ለሥራ የወጣለት ደረጃ በመካከለኛው ዘመን ይሁዲነት ውስጥ ጽኑ ስፍራ እስከ መያዝ ደርሶ ነበር። አንድ የአይሁድ የረበናት ትምህርት ቤት፣ ሥራ ለመንፈሳዊ ሕይወት ወይም ነገር የሚሰጠውን ጊዜ ስለሚሻማ ኰንኖታል ("ውጉዝ ከመ አርዮስ" ብሎታል)። ታልሙድ በሚባለው መጽሐፍ ላይ የሰፈረው የአይሁድ ረበናት ጸሎት እንዲህ ይነበባል፡- "አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤ የዕጣ ክፍሌን እንደ ሌሎቹ ሳይሆን ቃልህ (ቶራህ) በሚነገርበትና በሚተነተንበት ስፍራ ስላደረግኸው አመሰግንሃለሁ። እኔ ማለዳ ተነሥቼ ወደ ቤትህ እገሠግሣለሁ፤ እነርሱም ማለዳ ተነሥተው ወደ ሥራቸው ይሄዳሉ። እኔ ሌሊት ተነሥቼ የሕግህን ቃሎች እመረምራለሁ፤ እነርሱም ሌሊት ተነሥተው የዕለቱን ሥራቸውን ይሠራሉ። እኔ እስኪደክመኝ ድረስ ሕግህን አጠናለሁ፤ እነርሱም እስኪደክማቸው ድረስ ይሠራሉ። እኔ እስኪደክመኝ ባጠናም ብድራት አለኝ፤ እነርሱ ግን እስኪደክማቸው ሠርተው ብድራት የላቸውም እኔ እሮጣለሁ፤ እነርሱም ይሮጣሉ። እኔ የምሮጠው ወደ መጻኢው የሕይወት ዘመን ነው፤ እነርሱ የሚሮጡት ወደ ጥፋት ነው"[8]።*

*ሥራን "ቅዱስና ርኩስ" በማለት መከፋፈል የተጀመረው በአይሁዳውያኑ ባይሆንም፣ እሳቤው ዘመኖችንና ትውልዶችን እያቋረጠ ሲሄድ በየደረጃው የመጕልበትና የመርቀቅ ዕድል ገጥሞታል። ከረበናቱ ጸሎት እንደምንረዳው ሥራ ደረጃ ወጥቶለታል፤ ሠራተኞችም ደረጃ ወጥቶላቸዋል። "ቅዱስ ሥራ" የሚሠሩ ብድራታቸው ሕይወት ነው። ባንጻሩም "ርኩስ ሥራ" የሚሠሩ ብድራታቸው ጥፋት ነው።*

## 1.4. *ሥራ በኢትዮጵያውያን ዘንድ*

*እኛ ኢትዮጵያውያን ለሥራ ያለን አመለካከት እጅግ ዝቅተኛ ነው ቢባል ዕብለት አይሆንም። ለዚህም ባህላችን የሚመራበት ሥርዐት፣ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ለመገመት አያዳግትም። ባህላችን ክቡር ባንጻሩም ውሩድ የሚለው ነገር አለው። በሌላ አነጋገር ነገሮችን የምንመለከተው በሁለት ዐቢይ ወገን መድበን ነው። በአንዱ ወገን "የተከበሩ" የምንላቸው ነገሮች አሉን፤ በሌላው ወገን "የተዋረዱ" የምንላ ቸው ነገሮች አሉ። ነገሮችን የምናየው በእነዚህ በኩል ነው። ለሥራም ያለን አመለካከት እጅግ ዝቅተኛ የሆነው፣ አንዱን ሥራ ክቡር ሌላውን ሥራ ውሩድ ስለምንል ነው[9]። ኢትዮጵያ ማንኛውም ዐይነት ሥራ የሚከበርባት አገር አይደለችም። ለሥራ ያወጣነው ደረጃ ልበ ሙት (ሐሳቡ የሞተ፣ ከሥራ የቦዘነ) አድርጎናል። የስንፍናም መዐት እጅግ ነግሦ ብናል።*

---

[8] Joachim Jeremias, *Rediscovering the parables* (New York: Scribner, 1966), 113.

[9] ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ *አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ* (አሥመራ፤1912) ገጽ 17።

*እና ታዲያ ብንራብ፣ ብንጠማ፣ ብንታረዝ ምን ያስደንቃል? የደኻ ደኻ ብንሆንስ ምን ያስገርማል?*[10]::

**ጥ***ንታውያኑ ሕዝቦች ሥራን* "ቅዱስ-ርኩስ" (*መንፈሳዊ-ዓለማዊ፣ ሰማያዊ-ምድራዊ*) በማለት ደረጃ አውጥተውለት ነበር:: እኛ ደግሞ "ክቡር-ውሩድ" ብለን ሌላ ደረጃ አወጣንለት:: የመጀመሪያውን በቤተ ክህነት አካባቢ ገኖ የምናገኘው ሲሆን፣ ሁለተኛውን ደግሞ በሕዝቡ አካባቢ ገኖ እናገኘዋለን:: እንግዲህ ስንፍናውና ሥራን የመጥላቱ ዐመል ያለው በሁሉም ዘንድ ነው:: ስንፍና ያፈዛል፤ ያደንዛል፤ ያደነቊራል:: ልበ ሙትነቱና ልበ ልልነቱ ከየትም የመጣ አይደለም - ለሥራ ካወ ጣነው ደረጃ እንጂ::

**እ**ዚህ ላይ ጥቂት አብነቶችን ወስደን ብንነጋገር የሚበጅ ይመስለናል:: ባህላችን "ሥራ ሙት ባህል" (ሥራ የሞተበት) ነው ስንል ወሬ እንጂ ሥራ አይወደድበትም፤ ምላስ እንጂ ሥራ አይከበርበትም ማለታችን ነው:: ለምሳሌ በስብሰባዎች ላይ ተቀምጠን ስንነጋገርና ስንወያይ ብዙ ጊዜያችን የሚጠፋው ስንካሰስና ስንዋቀስ ነው:: አሉ የሚባሉ ችግሮች አንድ በአንድ ተነሥተው ለችግሮቹ ተገቢ መፍትሔ ሲፈለግ አይታይም:: መፍትሔ መፈለጉ ቢሳካልን እንኳ፣ ነገሩን ተርግባራዊ ለማድረግ ቊርጥ ውሳኔ ስናደርግና ስንጥር አይታይም:: ሁሉን ነገር የምንተወ ው ለእነ እከሌ ነው:: እኔ ይሄን አደርጋለሁ አንልም:: የነገር መንገድ (ልዩ ልዩ ስልት) አለማወቃችን ብቻ ሳይሆን፣ ለሥራ ታጥቀን አለመነሣታችንም ትልቁ ችግራችን ነው:: ከዚህም የተነሣ ባህላችን "ወሬ ምሳው" ባህል ሆኗል:: እንደ እውነቱ ከሆነ "የወሬ መንደሮችና የወሬ ቋቶች" ነን:: ችግር ለመፍታትና አገር ለመገንባት የምንፈልገው በወሬ ነው:: በጥቅሉ ተግባረ ቢስ ሕዝቦች ነን:: ሥራ በሚከበርባቸው አገሮች ታላላቅ ሥራ ያከናወኑ ሰዎች የታሪክ አባት፣ የዘመናዊ ሳይንስ አባት፣ ወዘተ የሚል ስም ይሰጣቸዋል:: ለእኛ ስም ይሰጠን ከተባለ ተስማሚው ስማችን "የወሬ አባት" የሚለው ነው[11]:: ለዚህ አባባል ሁነኛና እውነተኛ ታሪክ መጥቀስ ተገቢ ይሆናል:: ለጊዜው ሁለት ሰዎች የተናገሩትን እንጠ ቅሳለን::

**አ**ንደኛው ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ናቸው:: "አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ" በተሰኘው ድንቅና አነስተኛ መጽሐፋቸው ላይ፣ የእኛ የኢትዮጵያውያንን የሥራ ባህል በእግረ መንገዳቸው እያነሡ በብርቱ ኰንነዋል:: ጸሓፊው ሌሎች ሕዝቦች በተለይም አውሮፓውያን ምን ያህል ሠራተኛ ሕዝብ እንደ ሆኑ ከእኛ ጋር ሲያገናዝቡት እጅግ

---

[10] በዚህች ምድር ላይ አሉ ከሚባሉት 49 ፍጹም ደሀ አገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት:: በአሁኑ ጊዜ 46% የሚሆነው የአገሪቱ ሕዝብ (ወደ 26 ሚሊዮን የሚሆነው) የቀን ገቢው ከአንድ ዶላር በታች ነው:: ጥናታዊ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያ ከዚህ ድህነቷ ለመውጣት 100 ዓመት ያስፈልጋታል፤ ለዚያውም አሁን እያሳየች ነው በተባለው የ7% ዕድገት ከቀጠለች:: አለበለዚያ ነገም ጨለማ ነው:: በዚህ ላይ ብርሃኑ ነጋ እና ሰይድ ኑሩ" *Performance of the Ethiopian Economy 1991-1998* " በሚል ርእስ ያቀረቡትን ጥናታዊ ጽሑፍ ያነቧል (The Ethiopian Economy: Performance and Evaluation፤ ገጽ 19-47)::

[11] አባባሉ ቅር የሚያሰኝ ከሆነ ይቅርታ እንጠይቃለን:: የሚበጀን ግን የሆነውን ነገር በግልጽ መነጋገሩ ነው:: የሆነውን እንዳልሆንን፣ ያልሆነውንም እንደሆንን ብንናገር ምንም አይጠቅመንም:: ባህላችን ሠራተኛነትን እንደማያበረታታ እየታወቀ ነገሩን አድበስብሰን ብናልፍ እውነት በእኛ ዘንድ የለችም:: ክርስትና አስመሳይነትን አጥብቆ ይኰንናል:: "የወሬ መንደር" ማለት እውነቱና ሐሰቱ ያልተለየ ወሬ የሚወራበት መንደር ማለት ነው:: "የወሬ ቋት" ማለት ደግሞ ከአፉ ላይ ወሬ የማይጠፋበት ሁልጊዜ ወሬ የሚያወራ ማለት ነው (ከሣቴ ብርሃን ተሰማ መዝገበ ቃላት፤ገጽ 932)::

ይንገበገቡ ነበር። በእርሳቸው ዘመን እንኳ በቅኝ ግዛት ሥር ከነበረችው ሱዳን፣ ነጻዪቱ ኢትዮጵያ ምን ያህል ወደ ኋላ እንደ ቀረች ሲያስቡት እርር ድብን ይሉ ነበር[12]።

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት እንደሚሉት እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ ከመፋጀት ሌላ ምንም ሥራ የለንም[13]። ከዛሬ 80 ዓመት በፊት የነበረንን አስተሳሰብ ሲገልጹ "የሰው ክብረቱ ሥራና አእምሮ መሆኑን ገና አላወቅነም" ብለዋል[14]። የሥራ ግቡና ትርጉሙ ገና ምንም እንዳልገባን የሚገልጽ ትልቅ ቁጭት ነው። "ባገራችን እስከ ዛሬ ድረስ ሠርተው ደክመው መብላት ነውር ነው" በማለት የተናገሩት በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም[15]። ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ከዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሱት በጭፍን አይደለም። የነገሥታቱን፣ የሹማምቱን፣ የወታደሩንና የገበሬውን ኑሮ ከመረመሩ በኋላ ነው። ከላይ እስከ ታች ሁሉም ሐኬተኛ እንደ ሆነ በሐዘን ገልጸዋል። ያቅሙን ያህል ትንሽ የሚጥረውና ሰነፉን ሕዝብ የሚቀልበው ያው ምስኪኑ ገበሬ እንደሆነም ጠቁመዋል[16]።

እኚህ ታላቅ ሰው ምናልባት ሰሚ ተገኝቶ የተባለውን ነገር ያስተውል ይሆናል፣ ብሎም የሚበጀውን መንገድ ይከተል ይሆናል በሚል ዐሥር ታላላቅ ምክሮችን በጽሑፋቸው መጨረሻ ላይ ለግሰዋል። ከምክራቸው መካከል በሥራ ላይ በቀጥታ ያተኰረ ባይኖርም፣ ምክራቸው ግን ቆም ብለን ግራና ቀኛችንን እንድናይ፣ እርምጃችንን እንድናስተውል፣ ምን እየሠራን እንደ ሆነ ራሳችንን እንድንጠይቅ የሚጋብዝ ነው፡ ውስጥ ውስጡን ግን "ትጉነትና ንቁነት" ባህላችን እንዲሆን በብርቱ የሚያሳስብ ነው። አለበለዚያ ገብረ ሕይወት እንደሚሉት "እንደመሰሳለን" [17]።

ገብረ ሕይወት "የእኛ የኢትዮጵያውያን ያለፈው ታሪካችን እጅግ ያሳዝናል " በማለት ያኔ ተናግረው ነበር[18] ። ከ80 ዓመት በኋላ ታሪካችን ያው የሚያሳዝን ታሪክ መሆኑን እርሳቸው ወዳሉበት ሄዶ የሚነግራቸው ሰው ቢኖር ቁጭታቸውና ሐዘናቸው እንደምን የከፋ ይሆን! እንደ ድሮው ሁሉ አሁንም እርስ በርስ እየተፋጀን ነው፤ እንደ ድሮው ሁሉ አሁንም ሐኬተኞች ነን፤ እንደ ድሮው ሁሉ አሁንም ከሌሎች አንማርም፤ እንደ ድሮው ሁሉ አሁንም "ሠርቶ ደክሞ መብላት" ነውር የሆነብን ሕዝቦች ነን። ነጋድራስ ገብረ ሕይወትን እንደ ነቢይ የሚያስቈጥራቸው አንድ ነገር ተናግረዋል። "ምነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዕንቅልፍህ መቼ ትነሣለህ"[19] በማለት የተናገሩት መቼም የማንለወጥ ሕዝብ መሆናችን ተገልጾላቸው ይሆን?

---

[12] ባህሩ ዘውዴ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966* ( አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ 1989) ገጽ 114።

[13] ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ *አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ* (አሥመራ፤1912)ገጽ 16-17።

[14] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 17።

[15] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 17።

[16] ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴም ከዚህ ሐሳብ ጋር ይስማማሉ። "*የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966*" በተሰኘው ድንቅ መጽሐፋቸው የገበሬውን ፍዳ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፣ "መሳፍንት ሥልጣን ሲቀራመቱ፣ ካህናት ጠጕር ሲሰንጥቁ የሥርዐቱ ተሸካሚ የሆነው ገበሬ እነዚህን ሁሉ ለመመገብ ይዳክር ነበር። የኀብረተ ሰቡ አምራች ክፍልም እሱው ብቻ ነበር። ዘር ቈጥሮ በሚያገኘው ርስቱ ላይ በሬውን ጠምዶ እያረሰና ከብቱን እያረባ ክረምት ከበጋ ሳይለይ ይለፋ ነበር። ይሁንና በምርቱም ሆነ በሥራ ሰዓቱ ላይ ሙሉ ቊጥጥር አልነበረውም። መሳፍንቱና ካህናቱ ከነገሥታቱ በሚያገኙት ጉልት አማካይነት ከገበሬው ልኩ ያልተደነገገ ግብር ይሰበስባሉ።... ገበሬው ለባለ ጉልቱ እህል ከመስፈር አልፎ ሁዳድ በማረስ፣ እህል በመፍጨትና ቤትና ጐተራ በመሥራት የጕልበት ሥራ እንዲያበረክት ይገደድ ነበር። ይህ የጕልበት ሥራም ካለው ጠቅላላ የሥራ ጊዜ ከሦስት አንድ እጁን ይወስድበት ነበር" (ገጽ 13)።

[17] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 24።

[18] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 18።

[19] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 19።

እንደ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ሁሉ ስንፍናችን ልክ የሌለው መሆኑን ከተረዱት ጥቂት ምሁራን መካከል አንዱ ከንቲባ ገብሩ ደስታ ናቸው። በአንድ ወቅት ለትምህርት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ሳለ የገጠሟቸውን ነገር እንዲህ በማለት ያወጋሉ፣ "ኢየሩሳሌም ትምህርት ቤት እንደ ገባሁ ሰሞን ከተማሪዎች ጋር የደረቀ ፍግ በአካፋ እየዛቅን በሚገፉ ጋሪ ወደያትክልቱ እንድናፈስ ታዘዝን። ተማሪዎቹ የለመዱት ሥራ ስለ ነበር እየተዝናኑ እየተጫወቱ ይሠራሉ። የክፍል አለቃዬ መጣና 'ኅባው አትሠራም እንዴ' ቢለኝ 'እኔ ፍግ ለመዛቅ አልመጣሁም ለመማር እንጂ!' ብዬ መለስሁለት። የክፍል አለቃዬ ይህንኑ ሄዶ ለዋናው አስተዳደር ነገራቸው። እሳቸውም 'ተውት ግድ የለም፤ እሱ የመጣው ሥራ መሥራት ካልለመደ አገር ስለሆነ እስኪላመድ ድረስ አትንኩት' ብለው ሲናገሩ ሰማሁ። እኔም ጥቂት ደቂቃዎች ከቆየሁ በኋላ ቈጨኝና የሚገፋውን ጋሪና አካፋዬን ይዤ እንደ ጓደኞቼ እየተሻማሁ መሥራት ጀመርሁ። ከዚያ በኋላ ሥራ ሕይወት መሆኑን ተማርሁና ኑሮዬን ማቃናት ቻልሁ"[20]። መቼም ካልጠፋ ነገር በስንፍና መታወቃችን እጅግ ያሳዝናል። ከሁሉ የሚያሳዝነው ግን አሁንም ስንፍና መታወቂያችን መሆኑ ነው። ያለንበት ሁኔታ አንገብግቦን ለሥራ የምንነሣው መቼ ይሆን?

ሥራ ክቡርና ውሩድ በሚባልበት አገር፣ ስንፍናና ልመና መናኘቱ አይቀርም። ኢትዮጵያ ማንኛውም ሥራ ተከብሮ፣ በቅን ፍላጎት የሚሠራባት አገር አይደለችም። በራስ ጥረት ከሚገኝ እንጀራ ይልቅ፣ በልመና ወይም በውንብድና የሚገኝ እንጀራ ያምረናል። በገዛ እጃችን ሠርተን ከመብላት ይልቅ፣ ሌሎች ደክመው ያገኙትን ብንበላ ደስ ይለናል። በእኛ አገር የተገኘውን ሥራ ሠርቶ መኖር እንደ ውርደት፣ ልመና እንደ ጌጥ ተቈጠሯል። ሥራ ተንቆ ልመና ተወድሷል። ሳንሠራ ለመብላት እንፈ ልጋለን፤ ሳንደክም ለመክበር እንፈልጋለን። ተቃርኖው አቻ የለውም እኮ። በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ሥራ ፈትነት ውጉዝ እጅግ ውጉዝ ነው። በዚህ አምላክ ዓለም ውስጥ ሥራን በተመለከተ ሁለት መርሖች አሉ - አዎንታዊና አሉታዊ። አዎንታዊው መርሕ "የሚሠራይብላ" ይላል (1ተሰ 4÷11)። አሉታዊው መርሕ "የማይሠራ አይብላ" ይላል (2ተሰ 3÷10)።

በ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር፣ አንድ ዐቢይ ዐውደ ጥናት አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ዐውደ ጥናት ላይ ከቀረቡት ጽሑፎች መካከል ሦስቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ድህነት ቅነሳ የሚያወሱ ነበሩ። አንደኛው ጸሓፊ"መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ ልማትና የድህነት ቅነሳ ሰነድ"[21] በሚል፣ ሁለተኛው ጸሓፊ "የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ"[22] በሚል፣ ሦስተኛው ጸሓፊ ደግሞ "የድኽነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ፅንሰ ሐሳብና አዘገጃጀት ሂደት"[23] በሚል ዝርዝር ሐተታ የያዙ ጽሑፎችን አቅርበዋል። ጸሓፊዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ድህነት ለመቀነስ (ከተቻለም ለማጥፋት) ይረዳሉ ያሏቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች በሚገባ ተንትነዋል። ጸሐፊዎቹ ያቀረቧቸው የመፍትሔ ሐሳቦች፣ ሰሚ አግኝተው በሥራ ላይ ቢውሉ፣ ድኽነታችን ሊቀንስ ብሎም ሊጠፋ እንደ ሚችል ምንም ጥርጥር የለንም። የመፍትሔ ሐሳቦቹ ብዙ መልካም ነገር አካተዋል። ጸሓፊዎቹ "ሥራንና ሠራተኛነትን" በተመለከተ

[20] ኰሎኔል ዳዊት ገብሩ፣ *ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵ ቅርስ* (አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት 1985) ገጽ 22 ።

[21] ዶ/ር ሽመልስ ተ/ጻዲቅ (Ethiopian Economic Association ፤ መስከረም 1994 አዲስ አበባ)።

[22] ዶ/ር ወልዳይ አመሐ (Ethiopian Economic Association ፤ መስከረም 1994 አዲስ አበባ)።

[23] ሰኢድና ጌታሁን (Ethiopian Economic Association ፤ መስከረም 1994 አዲስ አበባ)።

ምንም ነገር አለመጥቀሳቸው ግን እጅግ አስደንቆናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደኸየው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች ስላሉበት ብቻ ነው? እርግጥ እነዚህ ነገሮች እንደ አንድ ምናልባትም እንደ ትልቅ ምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ፤ ደግሞም ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ስንፍናችን አላደኸየንም? ሥራ ሳይሆን ወሬ ወዳድነታችን አላቈረቈዘንም? በጥናት ጽሑፎቹ ውስጥ "ሥራን እንውደድ! ሥራን እናክብር! ሠራተኛ ሕዝብ እንሁን!" የሚሉ ሐሳቦች አለመስተጋባታቸው እጅግ ቢያስገርመንም፣ ከመፍትሔ ሐሳቦቹ መካከል የሥራ ባህላችንን የሚመለከቱ አስተያየቶች የግድ መኖር ነበረባቸው እንላለን፡፡

ያም ሆነ ይህ ለስንፍናችን፣ ለሥራ ፈትነታችንና ለወሬ ስንቁነታችን ተጠያቂው ማን ነው? የሚል ጥያቄ ለማንሣት እንወዳለን፡፡ እንደ እኛ እንደ እኛ በመጀመሪያ መንፈሳዊ መሪዎቻችን ናቸው፤ ሊያስተምሩን ሲችሉ አላስተማሩንም፡፡ ቀጥሎ ቤተሰቦቻችን ናቸው፤ ሊመክሩን ሲችሉ አልመከሩንም፡፡ ከዚያም መምህሮቻችን ናቸው፤ ሊያሠለጥኑን ሲችሉ አላሠለጠኑንም፡፡ በመጨረሻም እኛው ራሳችን ነን፤ የስንፍናውን መጥፎ ባህል መስበር ስንችል በደስታ ተቀብለን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ተሰናድተናል፡፡ ስንፍና ይበቃል የሚለን፣ ልመና ነውር ነው የሚለን፣ ነገር ግን በገዛ እጅ ሠርቶ መኖር ክብር ነው የሚለን ከቶ ማን ይሆን!!! ነውር መሆኑን አበክረው የነገሩንን ሰዎችስ (ለምሳሌ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝንና ከንቲባ ገብሩ ደስታን) በትሕትና የምንሰማቸው ከቶ መቼ ነው!!!

## 2. ሥራ በብሉይና በአዲስ ኪዳን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲነገር ከእግዚአብሔር ጋር ተያይዞ ነው የተነገረው፡፡ በዚያ የመጀመሪያው መጽሐፍ ውስጥ አንድ ታታሪ ሠራተኛ ለፍጥረቱ መልክ ሲሰጥ፣ ሥርዐት ሲያበጅና በአምሳሉ ለፈጠረውም ሰው ምሳሌ ሲሆን እናያለን፡፡ እግዚአብሔር እንደ ግሪካውያኑ አማልክት ተንፈላሶ መኖርን አይችልበትም፡፡ ጸተኛነትንም ሆነ ቸልተኛነትን አያውቅበትም፡፡ እርሱ ሁል ጊዜ ንቁ ነው፤ ዘወትር በሥራ ላይ ነው፡፡ በመፍጠር ብቻ ሳይሆን በመቤዠት ሲተጋ እናየዋለን፡፡ ፍጥረቱን በመንከባከብ፣ በመጠበቅና ሲስት ደግሞ በመመለስ ሲበረታ እናየዋለን፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሱን አምላክ ከሌሎች አማልክት የሚለየውም ይህ "ሠራተኛነቱ" ነው፡፡ በቅድሚያ በብሉይ ኪዳን ስለ ሥራ የተነገረውን በጥቂቱ እን መልከት፡፡

### 2.1. ሥራ በብሉይ ኪዳን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሥራ ምን እንደ ሆነ ከመነገሩ በፊት አንድ ትጉ ሠራተኛ በብርቱ ሥራ ተጠምዶ ይታያል፡፡ እርሱም "ሠራተኛው እግዚአብሔር" ነው፡፡ በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ሥራ የሚባል ነገር እንዳለና ይህም ሥራ ክቡር እንደሆነ የምንረዳው ከራሱ ከእግዚአብሔር ነው፡፡ በመጽሐፈ ዘፍጥረት የመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ "ፈጠረ፣ ለየ፣ አደረገ" (1÷1፡7፡11) የሚሉ ቃላትን እናነባለን፡፡ እነዚህ ሥራንና ተግባርን የሚያሳዩ ቃሎች እግዚአብሔር ሠራተኛ አምላክ መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ እግዚአብሔር በየቀኑ የሚሠራው፣ የሚከውነውና የሚፈጥረው ነገር ነበረው፡፡ ሲሠራ እንጂ እንደ ግሪካውያኑ አማልክት ሲንፈላሰስ አናየውም፡፡ ሲከውን እንጂ እንደ ምሥራቃውያኑ አማልክት ሲያንቀላፉ አናየውም፡፡ ሲፈጥር እንጂ እንደ ዘመኑ ምድራውያን ሲለግምና ሲቦዝን አናየውም፡፡ በአንድ ወቅት የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች "ለመሆኑ እግዚአብሔር ቀኑን ሙሉ ምን ሲሠራ ይውላል? " ብለው እንደጠ

የቁት፣ እኛም ጥያቄውን ብናነሣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን መልስ "ብዙ እጅግ ብዙ" የሚል ነው።

ለሥራ ትርጕም የሰጠው አምላክ፣ እርሱ ራሱ ብርቱ ሠራተኛ ነው። የሥራ አባት እንደሆነ ሁሉ፣ የሥራም ምሳሌ ነው። በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ቀጥሎም ብርሃንና ጨለማን ደነገገ። ከዚያም የብስንና ባሕርን ሠራ። ደግሞም የሰማይ አካላትንና እንስሳትን አበጀ። በመጨረሻም የፍጥረቱ ቁንጮ የሆነውን ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው (ዘፍ 1)። ከእነዚህ ክዋኔዎችና ተግባሮች እንደምንረዳው እግዚአብሔር "የሥራ አምላክ" ነው[24]። መዝሙረኛው ምስክርነቱን ሲሰጥ "የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" (19÷1) ይላል። በሌላም ስፍራ ሰማያት የእጁ/የጣቱ ሥራዎች እንደ ሆኑ ይገልጻል (መዝ 8÷3)።

ስለ ሥራ በምንነጋገርበት ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔርም መነጋገር ግድ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው። ሥራ የሰዎች ግኝት አይደለም። ከእግዚአብሔር የተገኘ አምላካዊ በረከት ነው። በመሆኑም በአምሳሉ ለፈጠረው ሰው ሥራን ሰጠው (ዘፍ 1÷28)። እርሱ ቦዘኔ ስላልሆነ ሰውም ቦዘኔ እንዲሆን አይፈልግም። ይልቁንም የዔድንን ገነት (የአትክልት ቦታ) ካዘጋጀ በኋላ የፈጠረውን ሰው በዚያ እንዲኖር አደረገው - እንዲያበጀው፤ እንዲጠብቀው እንዲከባከበው (ዘፍ 2÷8-15)። ሥራው ብዙ አምላክ ለሰዎችም ብዙ ሥራ ሰጠ። አሁን አዳምና ሔዋን ዘር መዝራትና ምድርን ማልማት አለባቸው (ዘፍ 2÷5)፤ የከበረ ድንጋይ ማውጣት አለባቸው (ዘፍ 2÷10-13)፤ የገዛ ምግባቸውን ማዘጋጀት አለባቸው (ዘፍ 2÷9)፤ ለእንስሳቱም ስም ማውጣት አለባቸው (ዘፍ 2÷19-20)። በዚህ ሁሉ ውስጥ የምናስተውለው አንድ ነገር አለ። ይኸውም በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ሥራ የተባረከ ተግባር ነው።

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን (ፍጥረታለምንና መላለምን) ካበጀ በኋላ፣ ሥራው በዚያው አላበቃም። አምላከኞነትን የሚከተሉ ሰዎች እንደሚሉት፣ ፊቱን ከፍጥረቱ አልመለስም። አምላከኛነት እንዲህ ይለናል፦ "ሰዓት አንድ ጊዜ ከተሞላ በኋላ በራሱ እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ እግዚአብሔርም ዓለምን ከፈጠረ በኋላ በራሱ ሕግ እንዲኖር አድርጓል»። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር ፍጥረቱን ዞር ብሎ አያይም፤ ወደ ፍጥረቱም አይመለከትም። የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ ግን እንዲህ አይደለም። እርሱ ፍጥረቱን የተወበትና ከፍጥረቱም የተለየበት ጊዜ የለም። እንዲያውም እርሱ ከፍጥረቱ ታሪክ ታጥቶ አያውቅም። እንደ መጀመሪያው ሁሉ አሁንም በሥራ ላይ ነው። ያኔ ያበጅ ነበር። አሁን ደግሞ ያበጀውን ይከባከባል። ያኔ ይፈጥር ነበር አሁን ደግሞ የፈጠረውን በሥርዐት ይመራል። እግዚአብሔር በርግጥም "ሥራ ብዙ አምላክ" መሆኑን የምናውቀው ሲፈጥር፣ ሲያድን፣ ሲፈርድና ሲቤዥ ስናየው ነው። ሥራው መላለምን በመፍጠር አላቆመም፤ ነገር ግን በታሪክ ሁሉ ቀጥሏል። እግዚአብሔር አይተኛም፤ አያንቀላፋም። ይልቁንም ሕዝቡን ዘወትር ይጠብቃል (መዝ 121÷3-4)።

በመጽሐፈ ዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር በመፍጠር ሥራ ተጠምዶ እናያለን፤ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በመጠበቅና በመከባከብ ሥራ ተጠምዶ እናያለን (ዘፍ1፤መዝ 104÷10-22)። ሌላ ጊዜ ደግሞ በመቤዠት ሥራ ተግቶ እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር እጅግ የሚታወቅበትን ተግባር መዝሙረኛው ሲገልጽ፦ "ለሰው

[24] Paul S. Minear," *Work and Vocation in Scripture"* in Work and Vocation: A Christian Discussion, ed. John Oliver Nelson (New York: Harper and Brothers, 1954), 44.

ልጆች ስላደረገው ተአምራት፣ ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑት" (107÷8 15÷21፡31) ይላል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ በጥቂቱ እንነጋገር።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ፊት ፊት እየሄደ የሕዝቡን ታሪክ ያቃናል፤ ያሳምራል። ሕዝቡ ሲስት ጨርሶ እንዳይጠፋ፣ የሚመለሱበትን መንገድ ያዘጋጃል። አብርሃምን ጠርቶ ተስፋ ሲሰጠው በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ እንደ ወሰነ ያሳያል (ዘፍ 12÷1-3)። ከዚህ በኋላ ባለው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ተሳትፎ እየጎላ ሲሄድ እናያለን። ከአብርሃም ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን፣ በአንድ በኩል ሕዝቡን በሌላ በኩል ደግሞ ምድሩን ያካትታል። ሊቤዥ ያሰበው ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን፣ ምድሩንም ጭምር ነው።

ወደ ፀአቱ ታሪክ ስንመጣ ደግሞ ተሳትፎው እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ በቀላሉ እናስተውላለን (ዘፀ 1-15)። የፀአቱ ታሪክ የሚያሳየን የያህዌን ብርቱ ክንድ (አቻ የለሽ ኀይል) ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ ቤዛዊ ሥራና ዐላማ ጭምር ነው። ያህዌ እስራኤልን ነጻ ባወጣ /በተቤዠ ጊዜ አራት ነጻነቶችን አጐናጽፎአታል። እነዚህን አራት ነጻነቶች ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን[25]። በፖለቲካዊው ረገድ ጨቋኝና አምባ ገነን ከሆነ ባዕድ መንግሥት ተቤዥቷታል። በማኅበራዊው ረገድ ቤተሰባዊ ሕይወቷን ከሚያተራምሱ ሕዝቦች ተቤዥቷታል። በኢኮኖሚው ረገድ ከበዝባዥ አሠሪዎች ተቤዥቷታል። በመንፈሳዊው ረገድ ከባዕዳን አማልክት አገዛዝ ተቤዥቶ ያህዌን አምላኪ አድርጓታል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በዚህ ዐይነት መንገድ ከተቤዠና በሲና ተራራ ላይ ሕጉን ከሰጠ በኋላ (ዘፀ 20-24)፣ ለራሱ የሚሆን የተለየ ሕዝብ መፍጠር ጀመረ። ሐሳቡ "ካህናት" ማለትም ለሌሎች ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎችን ለመፍጠር ነው (ዘፀ 19÷4-6)።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ታሪክ ተለይቶ እንደማያውቅ ይበልጥ ከሚያረጋግጡ ልን ነገሮች መካከል፣ "የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከልን" (ገላ 4÷4) የሚለው አንዱና ትልቁ ነው። በታሪካችን ውስጥ ያለፈባቸውን መንገዶች በጥንቃቄ ተከትለን ስንሄድ "ቃልም ሥጋ ሆነ" (ዮሐ 1÷14) ከሚለው ላይ ስንደርስ "ዱካው" የእርሱ መሆኑን እንገነዘባለን። በመሆኑም "ታሪክ" ሳይሆን መባል ያለበት "ታሪኩ" ነው (ፈረንጆቹ Not History but His Story እንደሚሉት)። እግዚአብሔር በመሲሑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መልበሱ ሁለት ታላላቅና አዳዲስ ነገሮችን አስከትሏል። አንደኛው የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች ሕይወት/ታሪክ ውስጥ ብርቱ ሥራ ለማከናወን እንደ ተገለጠ ያስገነዝባል። በኢየሱስ ቃሎችና ሥራዎች እንዲሁም በተከታዮቹ ተልእኮ የተገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት የሰዎችን ሕይወት፣ ሐሳብና እሴት ለመለወጥ ታላቅ ኀይል አለው። ይኸውም ለወደቀውና ውጥንቅጡ ለወጣ ዓለም አዲስ መንገድ - የእግዚአብሔርን መንገድ - አስተዋውቋል።

ሁለተኛው የመስቀሉ መንገድ እግዚአብሔር የእኛን "መላ ታሪክ" ለመካፈል እንደ ወደደ ያስታውቀናል። ታሪካችን የውድቀት ደግሞም የተስፋ መቍረጥ፣ የሽሽት ደግሞም የግራ መጋባት ታሪክ ነው። እግዚአብሔር ሥጋ ለበሰ ሲባል፣ በዚህ ሁሉ ትግል ሊያግዘን ከጐናችን ቆመ፣ ተሰለፈ ማለት ነው[26]። ይህን ሁሉ ያነሣነው የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ በርግጥም ታታሪ ሠራተኛ መሆኑን አብነት ጠቅሶ ለመወያየት ያህል

[25] Christopher J. H. Wright, *Walking in the ways of the Lord: The Ethical Authority of the Old Testament* (Downers Grove: InterVarsity Press, 1995), 17-18.

[26] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 21።

ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው በፍጥረት ነው፤ የሚጨርሰውም በአዲስ ፍጥረት ነው። አምላካችን ሥራ ፈት አምላክ አይደለም። ሠራተኛና የሥራ አምላክ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ያቀረበልን፣ ትጉ ሠራተኛ አድርጎ ነው። እግዚአብሔር ሥራ ወዳድ አምላክ ነው። ምንም እንኳ ሥራው የተለየ ቢሆንም፣ ለእኛ ሥራ ግን ምሳሌያችን ነው። የእግዚአብሔር ሥራ መፍጠርና ለፈጠረውም ነገር መልክና ሥርዐት መስጠት ብቻ ሳይሆን አልሚና ጠቃሚም ነው። ማለትም ሥራው ሌሎችን ይጠቅማል፣ ለሌሎችም በረከት ይሆናል። ይህም በአንድ በኩል የእግዚአ ብሔርን ባሕርይ ሲያስታውቀን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እኛም የምንሠራው ሥራ ከዚህ የተለየ መሆን እንደ ሌለበት ያገነዝበናል።

### 2.2. ሥራ በአዲስ ኪዳን

እንደ ብሉይ ኪዳኑ ያህዌ ሁሉ፣ ኢየሱስም ታታሪ ሠራተኛ ነበር። በአንድ ወቅት የተመሰከረለት አናጢ ነበር። በሌላ ወቅት ደግሞ ስመ ጥር መምህር ነበር። ከወንጌላዊያኑ ዘገባ እንደምንረዳው፣ ሥራ ፈቶ የቦዘነበት ጊዜ የለም። ሁልጊዜ ሲንቀሳቀስና በሥራ ተጠምዶ ሲተጋ እናነባለን። ስለ ራሱ ሲናገር "አባቴ ሁልጊዜ ይሠራል፤ እኔም እሠራለሁ" ብሏል (ዮሐ 5÷17)። ደቀ መዛሙርቱን ብዙ ጊዜ ሲያሳስባቸው የነበረው "ቀን ሆኖ ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ" (ዮሐ 9÷4) እያለ ነበር። እንዲያውም የእርሱ ምግብ "የላከውን ፈቃድ ማድረግና ሥራውንም መፈጸም" እንደ ሆነ አስታውቋል (ዮሐ 4÷34)። ይህ የሚያሳየን ማንኛውም ሥራ በሥላሴ ዘንድ የተከበረ መሆኑን ነው። ሥራው አናጢነት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ወንጌል ሰባኪነት ሊሆን ይችላል። የሥራው ዐይነት ምንም ይሁን ምን፣ ሥራ ግን ክቡር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በብዙ የሙያ ስሞች ተጠርቷል፡- ሸክላ ሠሪ፣ አትክልተኛ፣ ገበሬ፣ እረኛ፣ ግንበኛ፣ አንጥረኛ፣ እየተባለ ተጠርቶአል። በእነዚህ ስሞች በመጠራቱ አንድም ጊዜ አላፈረም። ይልቁንም ሰዎች ባወጡለት ስም ራሱን ይጠራ ነበር። ዳዊት ያህዌን "እረኛዬ" ብሎት ነበር (መዝ 23÷1)። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" (ዮሐ 10÷10) አለ።

በመንፈስ ቅዱስ፣ በሐዋርያቱና በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የምናየው ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የእነዚህን ሦስቱን ሥራ በሚገባ ዘግቦልናል። ጳውሎስ በ1ቆሮ 15÷58 ላይ የተናገረውን ብንጠቅስ እስከ አሁን ድረስ የተነጋገርንበትን ነገር ይሰበስብልናል: "የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ! ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ፤ ለጌታ ሥራ የምትደክሙት በከንቱ አለመሆኑን ዐውቃችሁ ሳታቋርጡ ዘወትር የጌታን ሥራ ለመሥራት ትጉ"። በዚህ ምንባብ ላይ "የጌታ ሥራ" የተባለው ስብከተ ወንጌል እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ይሁንና በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ "ቅዱስ - ርኩስ" የሚባል ነገር ባለመኖሩ ማንኛውም ሥራ የጌታ ሥራ ነው። ፍጥረት ሁሉ የእርሱ እንደ ሆነ፣ ሥራም ሁሉ የእርሱ ነው። በተሰማራንበት በማንኛውም መስክ የምንሠራው የጌታን ሥራ ነውና።

### 3. ሥራ ምንድን ነው?

ሥራ ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም የሥራን ትክክለኛ ትርጉምና ግብ የምናገኘው በዚህ ውስጥ ነው። በቅድሚያ ሥራን በተመለከተ

መነጋገር ለምን እንዳስፈለገ እንወያያለን። በእኛ እምነት ሥራን በተመለከተ መነጋገር ያስፈለገበት ሦስት ሁነኛ ምክንያቶች አሉ።

አንደኛው ኅብረተሰባችን ሥራን በተመለከተ ያለው አመለካከት የተምታታ ነው። አንዳንዶች ምናልባትም በጣም ጥቂት ሰዎች ሥራን ጣዖት አድርገውታል። ከሥራ ውጭ ሌላ ሕልም ወይም ዓለም የላቸውም። ከግማሽ በላይ የሚሆነው ጊዜያቸው የሚውለው ለሥራ ነው። በእኛ አገር ባይሆንም በምዕራቡ ዓለም በሳምንት ከ72 ሰዓት በላይ የሚሠሩ ሰዎች እንዳሉ ይነገራል። ሌሎች ደግሞ ምናልባትም እጅግ ብዙ ሰዎች ሥራን ፍርጃ አድርገውታል። ከዚህም የተነሣ የሥራ ባህልና ምግባር (work ethic) ወድቋል። ለመዝናናት የምናስበውን ያህል ለመሥራት አናስብም። እናም ሳምንቱ አልቆ ዐርብ ሲመጣ እጅግ ደስ ይለናል። ሰኞ ሲመጣ ደግሞ ክፍት ድብር ይለናል። ሥራ የሚባለው ነገር ለብዙዎቻችን ዕዳ ነው። "እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰኞ ስለ መጣ ተመስገን" የምንል እንኖር እንደ ሆን አናውቅም። እንግዲህ በአንድ በኩል ሥራን አምላኪ በሌላ በኩል ደግሞ ሥራን ጠይ ሰዎች ነን። ሁለቱም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ እሳቤዎች ናቸው።

ሁለተኛው በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሥራን በተመለከተ ትምህርት ሲሰጥም ሆነ ሲመከር አይታይም። በእኛ ዕድሜ እንኳ ስለ ሥራ ሲነገርም ሆነ ሲሰበክ የሰማንበት ጊዜ እንዳለ ትዝ አይለንም። ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትም የሚታይ ትልቅ ውድቀትና ድክመት ነው። ለመጀመሪያዎቹ ፕሮቴስታንቶች በተለይም ፒውሪታንሶች ግን፣ ሥራ የተወደደ አርእስት ነበር። ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን ከዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር የማዛመድ ኀላፊነት አለባት። ከሁለትና ሦስት መቶ ዓመታት በፊት ግን ነገሩ እንዲህ አልነበረም። ሥራ የሚባለው አርእስት ከቤተ ክርስቲያን ከተወገደ ሰንብቶአል። ከዚህም የተነሣ ክርስቲያኖች ስለ ሥራ ያላቸው አመለካከት፣ ኅብረተሰቡ ካለው አመለካከት እምብዛም የተለየ አይደለም። ኅብረተሰቡ ሥራን ጠይ ኅብረተሰብ እንደ ሆነ ሁሉ ክርስቲያኑም ሥራን ጠልቶአል። በመሆኑም ሥራ መንፈሳዊና ዘላለማዊ እሴቱን አጥቶአል።

ሦስተኛው እግዚአብሔር ሥራን በተመለከተ ለሰዎች ሁሉ ያለው ዐላማ አንድ ወጥ መሆኑ አልተገለጸልንም። አብዛኛውን ጊዜ የተከበረው ሥራ መንፈሳዊ ሥራ ማለትም ቅስና፣ ድቁና፣ ወዘተ ይመስለናል። በሳምንቱ ቀናት ውስጥ ከሚሠራው ሥራ ይልቅ እሁድ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚሠራው ሥራ አቻ የሌለው ይመስለናል። ይህ ምናልባት እግዚአ ብሔር ለመንፈሳዊ ነገር እንጂ ለሰው ልጆች ሥራ ምንም ደንታ የለው ም ከሚል የመጣ ሳይሆን አይቀርም[28]። እግዚአብሔር ለመላው ዓለምና ለሰው ልጆች ሥራ በእርሱ መለኮታዊ ዕቅድ ውስጥ ምን ስፍራ እንዳለው በትክክል አልተገነዘብንም። እግዚአብሔር ለዓለሙ ሁሉ ዐላማ አለው። ይህ ዐላማ ምን እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ መልስ ይነጠናል። በሥነ ፍጥረቱ ሥርዐት፣ በኢየሱስ በተጀመረው መጻኢ መንግሥቱና በውጀት ታሪኩ ለሰው ልጆች ያለው ዐላማ ምን እንደ ሆነ አሳይቶአል[29]።

[28] Graham Dow, *A Christian Understanding of Daily Work* (Cambridge: Grove Books Limited, 2000), 3-4.

[29] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 6።

*እና እንግዲህ ሥራን በተመለከተ መነጋገር ግድ ሊሆን ነው:: በዚህ አርእስት ላይ ለመነጋገር ጊዜው ዐልፎ ይሆን የሚል ሥጋት ቢኖረንም፣ አሁንም ጊዜ አለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: ታዲያ ሥራ ምንድን ነው?*

*ደመወዝ እየተከፈለን ከምንሠራው ማንኛውም ሥራ ጀምሮ፣ የግል ንጽሕናችንን ለመጠበቅ የምንሠራውን ሁሉ ያካትታል:: ሥራ ሥጋዊና ማኅበራዊ ፍላጎታችንን የምንሞላበትና አምላካዊ ሕግን የምንፈጽምበት ተግባር ነው[30]:: ሰውን ከእንስሳ የሚለየው ነባቢና ለባዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ሠራተኛም መሆኑ ጭምር ነው:: ሥራ የሰው ልጆች መለያና መታወቂያ እንደ ሆነ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርልናል:: በዚህ ምድር ለሚኖሩ ሰዎች ሥራ ትልቁ ግብ ነው:: የሮማው ጳጳስ ዮሐንስ ጳውሎስ ሁለተኛ "ለሰው ልጆች ማኅበራዊ ጥያቄ መሠረታዊ ቊልፉ ሥራ ነው" በማለት የተናገሩትን ቃል በሙሉ ልብ የምንቀበለው ይመስለናል[31] :: ሥራ ምን እንደ ሆነ ይህን ያህል ከተነጋገርን፣ አሁን የምንሄደው ስለ ሥራ ባሕርይና ፋይዳ ወደ መነጋገሩ ይሆናል:: አሁን "ሥራ ለምን ትሠራለህ/ ትሠሪያለሽ?" ለሚለው ጥያቄ ሰዎች የሰጡ ትን ምላሽ እንመልከት፤[32]*

- *ሥራ የምሠራው ለመኖር የሚያስፈልገኝን ነገር ለማግኘት ነው:: የምበላውን፣ የምጠጣውን፣ የምለብሰውን፣ ብቻ በቤትም ሆነ ከቤት ውጭ የሚያስፈልገኝን ለማግኘት መሥራት አለብኝ::*

  *በዚህ አመላካከት መሠረት ሥራ የገቢ ምንጭ ሆኗል:: ይህም ሥራ በራሱ ያለውን ፋይዳ ከማጥፋቱም በላይ ሥራን ጣዖት ያደርገዋል::*
- *ሥራ የምሠራው ግድ ስለሆነብኝ ነው:: ጥረህ ግረህ ብላ ስለ ተባልሁ ሳልወድ በግድ እሠራለሁ:: ለመኖር ከፈለግሁ መሥራት አለብኝ::*

  *በዚህ አስተያየት መሠረት ሥራ ርግማን ሆኖአል:: ይህም ሥራ ማለት ዐፈር ደቼ መጋጥ ማለት ነው::*

- *ሥራ የምሠራው የጕልበቴን ዋጋ ለማግኘት ነው:: ጕልበቴን ለሚገዛ ለማንኛውም ቀጣሪ እሸጣለሁ::*

  *በዚህ አመላካከት መሠረት ሥራ ሸቀጥ ሆኖአል:: ይህም ሥራ በፋብሪካ ውስጥ እንደሚገኝ ማሽን ትርጕም የሌለው ነገር ነው:: የሚሸጠውና የሚገዛውም በገበያ ዋጋ ነው:: የዚህ መዘዙ ብዙ ነው:: ሰዎች ለሥራ ያላቸው ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል:: ሥራ ጥሪ መሆኑ ቀርቶ ገቢ ማግኛ ብቻ ይሆናል:: እናም ጥያቄው "ይህ ሥራ ምን መልካም ነገር ያስገኛል?" የሚል ሳይሆን "ይህ ሥራ ምን ያህል ክፍያ ያስገኛል? " የሚል ይሆናል::*

- *ሥራ የምሠራው የምሻውን/የምመኘውን ለማግኘት ነው:: በሌላ አነጋገር አካባቢዬ እኔ በምፈልገው መንገድ መደራጀት አለበት፤ የእኔ አሻራ መታተም አለበት::*

---

[30] Leland Ryken, *Redeeming the Time*, 229-232.

[31] Pope John Paul II, Laborem Exorcens ገጽ 4 as quoted in John R. W. Stott, *New Issues Facing Christians Today* (London: Marshall Pickering, 1999) ገጽ 188::

[32] Leland Ryken, *Redeeming the Time*, 15-21.

በዚህ አመላካከት መሠረት ሥራ ራስን መካቢያ ሆኖአል። ሥራ የሚሠራው ራስን ለማላቅ፣ ለማግነን፣ ከፍ ከፍ ለማድረግ ነው። የራስን ስም ለማስጠራትና ለራስ ሐውልት ለማቆም ነው።

- የምሠራው ርካታን ለማግኘት ነው። ሥራ ስሠራ ኅሊናዬ ይረካል፤ ውስጤም ደስ ይሰኛል። በሌላ አነጋገር ሰው እንደሆንሁ ይሰማኛል። ከሰው አንሼ እንዳልገኝ እሠራለሁ።

  በዚህ አመላካከት መሠረት ሥራ የበታችነት ስሜት ማስወገጃ ሆኖአል። ከሰው ላለማስና ከሰው ላለመነጠል ወደ ሥራ ይሄዳል።

- ሥራ የምሠራው ሌሎችን ለማገልገል ስል ነው። ሌሎችን ሳገለግል ደስ ይለኛል። ሌሎች ተጠቅመው ሳይ የመንፈስ ርካታ ይሰጠኛል።

  በዚህ አመለካከት መሠረት ሥራ አገልግሎት ሆኖአል። ሌሎች ከተጠ ቀሙ ሥራ ተሠርቶአል።

እነዚህ እንግዲህ ሥራን በተመለከተ የተሰጡ አስተያየቶች ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ከክርስቲያናዊው የሥራ ምግባር ጋር ተወራራሽነት እንዳላቸው ልብ ይሏል።

### 1.1. ሥራ ጥሪ ነው

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሥራ ደረጃ ወጥቶለት አናገኝም። ይህ ሥራ መልካም፣ ያ ሥራ መጥፎ ነው የሚል ነገር አናነብም። ይልቁንም ማንኛውም ሥራ እረኝነት ቢሆን፣ ሎሌነት ቢሆን፣ ክህነት ቢሆን፣ መሪነት ቢሆን፣ ግብርና ቢሆን፣ ንግሥና ቢሆን፣ ወዘተ የተከበረ ነው። በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ሥራ ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ክቡር ነው። ከውድቀት በኋላ ግን ይህ መሠረታዊ እሳቤ አምላካዊ ግቡን ስቶአል። እርግጥ ውድቀት ሥራን "መራራ ተግባር" አድርጎታል[33]። ምድር ራሷ ስለ ተረገመች (ዘፍ 3÷17-18 )፣ ከምድር የሚገኘውን ፍሬ ለመብላት ብርቱ ድካም ይጠይቃል። ከዚህም የተነሣ ስስት፣ ቀቀት፣ ምቀኝነትና በዝባዥነት ነገሠ። ይሁን እንጂ የመጀመሪያው አምላካዊ ግብ አሁንም አልተለወጠም። በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውና የተሰበከው የእግዚአብሔር መንግሥት/የእግዚአብሔር አገዛዝ የውድቀቱን ውጤት ማለትም መዘዝ ቀልብሶታል። መራራ የሆነብንን ነገር ወደ ቀድሞው ግብ በመመለስ ጣፋጭ አድርጎታል። በመሆኑም ለክርስቲያኖች ማንኛውም ሥራ ክቡር ነው። ሥራችን ምንም ይሁን ምን ለጌታ ብለን በትጋት እንድንሠራ ተመክረናል። "ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ" (ሮሜ 12÷10)። በሥራችን ስንፍናን ማሳየት ከቶውን ተገቢ አይደለም።

እስካሁን የተባለውን ነገር ከሌላም አንጻር ማጤን ይቻላል። ቀደም ሲል ማንኛውም ሥራ ክቡር ነው ብለን ነበር። አሁን ደግሞ ማንኛውም ሥራ "ጥሪ" ነው እንላለን። ይህን አባባል ጠለቅ ብለን ከመመርመራችን በፊት፣ እኛ ራሳችን ማለትም ክርስቲያኖች ማን እንደሆንን መመልከት ይኖርብናል። "በመጀመሪያ እኛ ራሳችን የተጠራን ሕዝቦች ነን። የተጠራነው በማን ነው? የተጠራነው በእግዚአብሔር ነው። የተጠራነው ለምንድን

[33] Ben Patterson, *Work and Worship: Serving God in everything you do* (Reading: Cox and Wyman Ltd. 1987), 30.

ነው? የተጠራነው በዚህ ዓለም የእርሱ አገልጋዮችና የእርሱ ካህኖች እንድንሆን ነው"[34]። ይህን ሐቅ ጴጥሮስ በግልጽ ሲነግረን፣ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠ ራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1ጴጥ 2÷9) ይለናል። ቅዱስ ጴጥሮስ በዚህ ስፍራ እንደሚነግረን በአንድ በኩል የተጠራን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሥራም ያለን ሕዝቦች ነን። እንግዲህ ሥራ ለክርስቲያኖች "ተግባር" ሳይሆን "ጥሪ" ነው።

ሥራ ጥሪ ነው ሲባል ምናልባት ግር ሊለን ይችላል። በመጀመሪያ ጥሪ/መጠራት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት እንደ ገባ እንመልከት። ጥሪ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ መንገድ ገብቶ ይገኛል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለደኅንነት ወይም ለደቀ መዝሙርነት መጠራት እንዳለ እናነባለን። እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራው እርሱን እንዲከተል ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠ ራው፣ በል እንግዲህ የቀድሞ ሥራህን ሁሉ እርግፍ አድርገህ ተው አላለውም። አብርሃም ከተጠራም በኋላ እረኛ ነበር። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ፣ "ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው" (1ቆሮ 1÷9) ይላል። ይህ ጥሪ ከሌሎቹ ሁሉ ቀዳሚ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ለተለየ መንፈሳዊ አገልግሎት መጠራት አለ። ካህን፣ ነቢይና ሐዋርያ ለመሆን የተጠሩ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች የተለየ "ጸጋ" ከተሰጣቸው በኋላ፣ ለልዩ ልዩ አገልግሎት ይላኩ ነበር። ለምሳሌ ኢሳይያስ አንዱ ነቢይ ነበር (ኢሳ 6÷1-10)። ነቢያት የእግዚአብሔርን "ልዩ መልእክት" ተቀብለው ለሕዝቡ ያደርሱ ነበር (አሞ 7÷15)። ሌላው ሰው ጳውሎስ ነው። እርሱም የምሥራቹን ቃል እንዲናገር የተመረጠ ሐዋርያ ነበር (2ጢሞ 1÷11)።

ደግሞም ለሥራ መጠራት አለ። ለምሳሌ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ ተጠ ርቶ ነበር (ዘፀ 3-4)። የሙሴ ጥሪ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ መሪ እንዲሆን ነው። በተመሳሳይ መንገድ ዳዊትና ሳዖልም ተጠርተው ነበር (መዝ 78÷70-71፤ 1ሳሙ 15÷17)። በብሉይ ኪዳን ሕዝብን መምራት ከእግዚአብሔር የሚገኝ ጥሪ ነበር። እንዲሁም የመገናኛውን ድንኳን እንዲያሳምሩ የተጠሩ ሰዎች ነበሩ (ዘፀ 31÷ 1-6)። እዚህ ላይ የጥበብ ሥራ ጥሪ ሆኖ እናገኘዋለን። ጳውሎስ ወንጌሉን እየሰበከ፣ ድንኳኑንም እየሰፋ ያገለግል ነበር። ጳውሎስ ሐዋርያ እንዲሆን ሲጠራ፣ ድንኳን መስፋቱን አላቆመም። ኑሮውን ይደግፍ የነበረው ድንኳን እየሰፋ ነበር (1ቆሮ 9÷12-15)። ለአንዱ መጠራቱ ሌላውን እንዲንቅ አላደረገውም። ሁለቱም ማለትም ወንጌልን መስበክና ድንኳን መስፋት ጥሪዎች ነበሩ። እግዚአብሔር ጳውሎስ ወንጌልን በሚሰብክበት ጊዜ ደስ እንደሚሰኝ ሁሉ፣ ድንኳንም ሲሰፋ ደስ ይለዋል። ምክንያቱም ሁለቱም በአንዱ በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ የሚገኙ ተግባሮች ናቸው። እንዲያውም ጳውሎስ ሥራውን አሞግሶ ተናግሮአል (2ተሰ 3÷7-9)።

እንደ ሉተርና ካልቪን የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች ተነሥተው የእነ ጳውሎስ ትምህርት ትክክል መሆኑን እስከ መሰከሩበት ጊዜ ድረስ፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት መጠራት ሌላውን እንደሚያስንቅ ይቈጠር ነበር። የተሐድሶው መሪዎች ስለ ሥራ የተናገሩትን ነገር ለማመስገን ከእነርሱ በፊት የነበሩ የጥንት ክርስቲያኖች በተለይም ከ300-600 ዓ.ም የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሰጡትን አስተያየት መመልከት ይኖርብናል። አውሳቢየስ ዘቂሳርያ የተባለ ሰው የክርስቲያን ሕይወት ለእግዚአብሔር አገልግሎት

[34] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 54።

የተለየ በመሆኑ ከጉልበት ሥራ መራቅ አለባቸው ይል ነበር። ለመኖር ሥራ የሚሠሩ ክርስቲያኖች "ሁለተኛ ደረጃ ክርስቲያን" ለመሆን የወሰኑ ናቸው። በዚህ ዓለም ለመኖር ሥራ መሥራት፣ ክርስቲያኖች የተጠሩበትን "የመጀመሪያ ደረጃ ክርስቲያናዊ ሕይወት" መናቅ ነው። ክርስቲያኖች የተጠሩት ለመንፈሳዊ ሥራና አገልግሎት እንጂ ለምድራዊ ሩጫ አይደለም። በመካከለኛው ዘመንም የነበሩ ክርስቲያኖች የሥራን ክቡርነት አጣጥለውታል። ክርስቲያኖች ስለ ሥራ ሊጨነቁም ሆነ ሊጠበቡ አይገባም። እነርሱን ሊያስጨንቃቸውም ሆነ ሊያስጠብባቸው የሚገባው፣ "የመንፈሳዊ አገልግሎት" ጉዳይ ነው[35]። ይህ የሚያሳን ከመንፈሳዊ ተግባር ውጭ ያለው ሥራ በጥንትና በመካከለኛው ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖች ዘንድ "የተናቀ ተግባር" መሆኑን ነው[36]።

ኢራስመስ ከዚያም ሉተርና ካልቪን ይህን አስተሳሰብ ክፉኛ ተቃውመውታል። እንደ ተሐድሶአውያኑ አባባል በዚህ ዓለም ማንኛውንም ሥራ እየሠሩ መኖር በእግዚአብሔር የተፈጠርንበትን ዐላማ እውን ያደርጋል። ማርቲን ሉተር ከዚህ በፊት ለሥራ የተሰጠው ትርጉም ትክክለኛ አለመሆኑን የገለጸው "ሥራ ጥሪ" ነው በማለት ነው። ይህም መላው ሕዝበ ክርስቲያንና አውሮፓ ለሥራ የተለየ ትርጉም እንዲሰጥ አድርጓል[37]። ለተሐሶአውያኑ ግን ከዚህ መለስ ያለው "ቅዱስ" ከዚያ መለስ ያለው ደግሞ "ርኩስ" አይደለም። ለእነርሱ በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር በጎና መልካም ነው። ሰዎች የሚሠሩት ማንኛውም ሥራ እግዚአብሔርን ያከብራል፤ ደስም ያሰኛል። ሥራ እንዲያውም "የምስጋና ፍሬ" ነው። ሉተር እንዲህ በማለት እንደ ተናገረው፣ "በዚህ ምድር የምንሠራው ማንኛውም ሥራ፣ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ሥራችን በቤተ ክርስቲያን ይሁን በቤት፣ በኩሽና ይሁን በእርሻ ሁላችንም እግዚአብሔርን እያገለገልን ነው"። ሥራ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን ቸርነት የምንገልጽበት መንገድ ነው። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት፣ የምናከብርበት፣ ሥራህ ሁሉ እንደምን ድንቅ ነው የምንልበት ነው [38]።

ስለ ጥሪ ስንነጋገር ጠሪ እንዳለ እየተናገርን ነው። ያም ጠሪ እግዚአብሔር ነው። ዓለምና በውስጧ ያለው ነገር በሙሉ የእግዚአብሔር ከሆነ፣ ሥራም የእግዚአብሔር ነው። የሥራ "ቅዱስ - ርኩስ" ወይም "ሥጋዊ - ዓለማዊ" የሚባል ነገር የለውም። ምክንያቱም ይህ ዓለም የእግዚአብሔር ዓለም ነው። መንፈሳዊውም ሆነ ሥጋዊው ዓለም የእርሱ ፍጥረትና ለእርሱም የተሠራ ነው። እግዚአብሔር ሥራውን አንድም ጊዜ አልኰነነም። ይልቁንም "እነሆ ሁሉም መልካም ነበረ" (ዘፍ 1) አለ። "ምድርና በምድር የሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው፤ ዓለምና በውስጥዋ ያሉት ሁሉ የእርሱ ናቸው" (መዝ 24÷1)። በመሆኑም ማንኛውም ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ ነው። እርሱ ለሥራችን ደረጃ አላወጣም።

---

35 ይህ አስተሳሰብ የጥንት ግሪካውያኑን ምንታዌ ማለትም "ቅዱስ - ረኩስ፣ መንፈሳዊ - ሥጋዊ፣ ሰማያዊ - ምድራዊ" የሚለውን እንደሚያንጸባርቅ ልብ ይሏል።

36 Alister MaGrath, *Reformation Thought: An Introduction* (Oxford: Blackwell Publishers, 2000), 266.

37 አውሮፓውያን በብዙ ረገድ ቢበለጽጉ ምንም አያስደንቅም። አንድ የታሪክ ሊቅ እንደ ተናገረው አውሮፓ በኢኮኖሚ ልታድግ የቻለችው የተሐድሶአውያኑን የሥራ ባህል ስለ ወረሱ ነው (Max Weber, *The Protestant Work Ethic and the Spirit of Capitalism* ይመለከቷል)።

38 Alister MaGrath, *Reformation Thought: An Introduction* (Oxford: Blackwell Publishers, 2000), 266-268.

## 1.2. ሥራ አምልኮ ነው

እግዚአብሔር ኅብረተሰብን ያዋቀረው ልዩ ልዩ ሙያ ባላቸው ሰዎች ነው። አንዱ ገበሬ ነው፤ ሌላው መሐንዲስ ነው፤ አንዱ እረኛ ነው፤ ሌላው መምህር ነው፤ አንዱ ወታደር ነው፤ ሌላው ንጉሥ ነው። አንዷ የቤት እመቤት ናት፤ ሌላው ሸማኔ ነው። እነዚህ ነገሮች ጥሪ ካልሆኑ ሌላ ምን ሊሆኑ ነው። ይህን አስመልክቶ የተጻፈ ግልጽ ምንባብ ቢኖር 1ቆሮ 7÷17-24 ነው። እርግጥ ይህን ምንባብ በተመለከተ አንዳንድ ሐቲታዊ ውዝግቦች አሉ ። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ለመናገር የፈለገው ስለ የትኛው ጥሪ ነው? ከዐውደ ምንባቡ እንደምንረዳው ሐዋርያው የሚናገረው ከድኅረ ድኅነት በፊት ስለ ነበረን ሁኔታ ነው። "እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር . . . በጠራው ጊዜ በነበረበት ሁኔታ ይኑር"። ጳውሎስ ይህን ሐሳብ በዚህ ምንባብ ውስጥ ሦስት ጊዜ ጠቅሶታል። እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር የተቀበለው ስጦታ አለው። ከዚህ ጋር ሉቃ 3÷12-14 ማገናዘብ ይቻላል። እንግዲህ ሥራ ጥሪ ከሆነ እግዚአብሔር ሥራ እንድ ንሠራ የሚፈልገው ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ብናነሣ ይበልጥ እያመራመረ ወደ ትክክለኛው ሐሳብ ይወስደናል።

አንደኛው ሥራ የምንሠራው ለእኛም ሆነ ለሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማግኘት ነው[39]። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሥራ ተሞግሶ፣ ስንፍና ግን ተወግዞ የምናገኘው በዚህ ምክንያት ነው (ምሳ 28÷19፤ 16÷26)። በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ ብርቱ ምክር ለክርስቲያኖች ሰጥቶአል። "...ሠርተው የራሳቸውን ምግብ እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛቸዋለን፤ እናስጠነቅቃቸዋለንም" (2ተሰ 3÷12)። ሥራ የሚያስፈልገንን ነገር የምናገኝበት መንገድ በመሆኑ "ሥራ ፈትነት" በእጅጉ ተኰንኖአል። "ያለ ሥራ መቀመጥ እንቅልፍን ያስከትላል፤ ስለዚህ ሰነፍ ሰው ረሀብተኛ ይሆናል"። "ትጉህ ገበሬ በቂ ምግብ ይኖረዋል፤ ጊዜን በከንቱ የሚያባክኑ ሰዎች ግን ሁል ጊዜ እንደ ደኸዩ ይኖራሉ" (ምሳ 19÷15፤ 20÷4፤ 20÷13)። በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ሥራ ፈት ሆኖ መኖር ፍጹም ነውር ነው። እያንዳንዱ ሰው በገዛ እጁ እየሠራ መብላት አለበት። የማይሠራ ከሆነ የጌታ ቃል እንደሚናገረው መብላት የለበትም።

ሁለተኛው ሥራ የምንሠራው የተፈጠርንበትን ዐላማ እውን ለማድረግ ነው[40]። ለመንቀዋለል አልተፈጠርንም፤ ለመቦዘንም አልተሠራንም። የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰው፣ እንደ እግዚአብሔር የሚሠራ ነው። በአምሳሉ ከፈጠረን በኋላ ሥሩ አለን (ዘፍ 1÷28)። ልብ እንበል "የምንሠራው ለመኖር አይደለም፤ ይልቁንም የምንኖረው ለመሥራት ነው"[41]። እግዚአብሔር ሠራተኛ ፍጡር አድርጎ ስላበጀን፣ እኛም እንሠራለን፤ እንፈጥራለን። የፈጠራ ክሂሎታችን ከየትም የመጣ አይደለም፤ ካተመብን አምሳሉ እንጂ። ሠራተኞች ከመሆን ይልቅ ቦዘኔዎች ከሆንን፣ ፈጣሪዎች ከመሆን ይልቅ አጥፊዎች ከሆንን፣ የተፈጠርንበትን ዐላማ ስተናል[42]። ሰው በፈጠራ ክሂሎት የተካነ ፍጡር ነው። ማሰብና ማስላት ይችላል፤ መማርና መመራመር ይችላል። በመሆኑም ሥራ ለሰው ልጆች መልካም የሆነው እነርሱነታቸው የሚታወቅበት በመሆኑ ነው። ሰዎች ኅሊናውያን እንጂ እንደ እንስሳት

---

39 Leland Ryken, *Redeeming the Time,* 229-232; 245-253.

40 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 229-232; 245-253.

41 Dorothy Sayers, *Creed or Caose*? In John R.W. Stott, New Issues Facing Christians Today (London: Marshall Pickering, 1999), 188.

42 John R.W. Stott, *New Issues Facing Christians Today* (London: Marshall Pickering, 1999), 189.

ደመ ነፍሳውያን አይደሉም:: ይልቁንም፣ "ለባውያነ ወንቁሃን" ናቸው:: ማለትም ብልኅና አስተዋይ ናቸው:: እንስሳት ግን እንዲህ አይደሉም:: እንደ እኛም "አምሳለ መለኮት" አይደሉም:: ሠራተኛነት ሰዎች በእግዚአብሔር የተፈጠሩበትን ዐላማ እውን ሲያደርግ፣ ሥራ ፈትነት ደግሞ ከዚያ ያጎድላቸዋል:: ለቧልትና ለዋዛ ፈዛዛ አልተፈጠ ርንም:: ሠራተኛ እንድንሆን ማለትም ሥራ አክባሪና በሥራ አዳሪ እንድንሆን ተፈጥረናል::

**ሦ**ስተኛው ሥራ የምንሠራው እርስ በርስ ለመደጋገፍ ነው[43]:: በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ኅብረተሰባዊነት እንጂ፣ ግለሰባዊነት ስፍራ የለውም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች አብረው እንዲኖሩ፣ እንዲሠሩ፣ እንዲተባበሩ ሲጠሩ ማየት የተለመደ ሥርዐት ነው:: አንዱ ሲሠራ፣ ሲያበጅና ሲያሳምር ሌላው ይጠቀማል:: የአንዱን ጒድለት ሌላው ይሞላል:: አንድ ሰው ሁሉን መሆን ስለማይችል፣ ለሁላችንም የተለያየ ችሎታ ተሰጥቶናል:: ሁላችንም በተሰጠን ችሎታ ስንሳተፍ አብረን ተደጋግፈን እናድጋለን:: ለሥራችን ትርጒም ከሚሰጠው ነገር አንዱ ይህ፣ "እርስ በርስ መደጋገፋችን" ነው:: ልብ እንበል! እርስ በርስ መደጋገፍ ተባለ እንጂ፣ ሽክም (ፓራሳይት) እንሁን አልተባለም:: ሥራ መተጋገዣና መረዳጃ መሆኑ ቀርቶ መበዝበዣና መጨቆኛ ከሆነ፣ "ራስ ወዳድነትን" እያራመድን ነው:: አዲስ ኪዳን በገዛ እጃችን እየሠራን ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን እንድንረዳ ይመክረናል (ኤፌ 4÷28)::

**በ**መጨረሻም ሥራ የምንሠራው ለፈጣሪያችንና ለአምላካችን ክብር እንዲሆን ነው[44]:: እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ዐላማና ግብ ሰጥቶአል:: ፍጥረቱ በተፈጠረበት ዐላማና ግብ ሲኖር እግዚአብሔር ይከብራል:: እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ተባባሪ ሠራተኞች እንድንሆን አድርጎናል:: ምድርን ሲፈጥር ምድር በራሷ ፍሬ እንድታፈራ አላደረገም:: ሰዎች ምድርን እንዲገዙና እንዲያለሙ አደረገ:: ይህም ከሰዎች ጋር አብሮ ለመሥራት ምን ያህል ራሱን ትሑት አንዳደረገ በግልጽ ያሳየናል:: እግዚአብሔር የሰዎችን "አብሮ ሠራተኛነት" ፈልጓል:: በሌላ አነጋገር "የሥራ ባልደረቦቹና አጋሮቹ" እንድንሆን ይሻል:: እርሱ ዐፈሩን፣ ዘሩን፣ ፀሓዩንና ዝናቡን አዘጋጀ:: እኛ ደግሞ እናርሳለን፣ እንዘራለን፣ እናጭዳለን:: እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፤ ሰዎች አልሚ ናቸው:: እግዚአብሔር አስገኚ ነው፤ ሰዎች ከእግዚአብሔር የተገኘውን እርሱ በሚሰጣቸው ጸጋና ኀይል ተንከባካቢ ናቸው፡፡ እንግዲህ በፈጣሪና በፍጡር መካከል "ትብብር" አለ ማለት ነው:: ስንሠራ እግዚአብሔርን እናከብራለን (1ቆሮ 10÷31፤ ቈላ 3÷23-24):: ሥራ አምላካዊ በረከት፣ ጸጋና ጥሪ ነው:: ስንሠራ በእግዚአብሔር የተፈጠርንበትን ዐላማ እንፈጽማለን፣ የእርሱንም አምሳል እንገልጣለን:: ሥራ Laborare est orare (ሥራ አምልኮ ነው) የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው:: እግዚአብሔር ስላለ ሥራ ክቡር ነው:: እግዚአብሔር ሠርቶ ስላሳየ ሥራ የተመሰገነ ተግባር ነው፡፡

## 4. ፀረ ሥራ አመለካከቶች

**ከ**ዚህ በመቀጠል ደግሞ ሰዎች ሥራን እንዴት እንደሚያዩትና እንደሚገልጡት በመጠኑ በመቃኘት ስለ ሥራ ክቡርነትና አስፈላጊነት እንነጋገራለን:: ሥራን በተመለከተ ወደ ሦስት የሚጠጉ አሉታዊ አመለካከቶች (ፀረ ሥራ አተያይ ልንላቸው እንችላለን) አሉ::

---

[43] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 191-192::
[44] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 192-195::

### 1.1. ሥራ ርግማን ነው

አንደኛው ሥራ ርግማን ነው[45]፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ክርስቲያኖች በዚህ ክፉ መርዝ ተነድፈዋል፡፡ "በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" የሚለውን ብሂል ልብ ይሏል፡፡ ለሥራ ያለን ግምት እጅግ ተዛብቶ ባለበት አገር ሥራ ርግማን ነው ብሎ ማስተማር እንደምን ጎሊናን መሳት ነው! ሥራ ርግማን ከሆነ አለመሥራት ወይም በመደበኛው አጠራር ቦዘኔነት በረከት ሊሆን ነው? ለማንኛውም እነዚህ ሰዎች ሥራ ርግማን ነው ሲሉ "እኛ ክርስቲያኖች ከርግማን ሁሉ ነጻ ስለ ወጣን የሥራ ሕግ አይገዛንም" ማለታቸው ነው፡፡ ርግማን ባይደርስብን ኖሮ "ጥረህ ግረህ ብላ" አንባልም ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች አሁን ከርግማኑ ነጻ ከወጣን በኋላ ጥሮ ግሮ መብላት የለም ባዮች ናቸው፡፡ "የንጉሥ ልጆች" አይሠሩም፤ አይለፉም፡፡ የንጉሥ ልጅ በመሆ ናቸው ሁሉ ነገር ይሰጣቸዋል፡፡ የሚያስፈልገንን ነገር ጠይቀን እናገኛለን እንጂ አንሠራም ይላሉ፡፡

### 4.2. ሥራ ፍርጃ ነው

ሁለተኛው ሥራ ፍርጃ ነው[46]፡፡ አንዳንዶች እንዲያውም ከአርባ ቀን ዕድል ጋር ያያይዙታል፡፡ የተፈጠርነው ለመሥራት ነው፡፡ ዶሮ የተፈጠረችው ለምንድን ነው ቢሉ መልሱ እንቁላል ለመጣል ነው፡፡ ዶሮ እንቁላሏን ለመጣል እንደምትሄድ ሁሉ እኛም ለሥራ እንሄዳለን፡፡ ዶሮ የተፈጠረችው ለሌላ ለምንም አይደለም ዕንቁላል ለመጣል፡፡ ሰው የተፈጠረው ለሌላ ለምንም አይደለም - ላቡን ጠፍ አድርጎ ለመፍጋት፤ ዐፈር ደቼ መጋጥ!

### 4.3. ሥራ ድካም ነው

ሦስተኛው ሥራ ድካም ነው[47]፡፡ በሌላ አነጋገር ሥራ ትርጉመ ቢስ ተግባር ነው፡፡ ትላንትም ሥራ፣ ዛሬም ሥራ፤ ነፍስ ካለች ነገም ሥራ፡፡ አሰልቺ በሆነ ዑደት ውስጥ ዝንተ ዓለም መዳከር፡፡ ማለቂያና ማብቂያ የሌለው ሥራ፡፡ ካልተሠራ የማይበላ ከሆነ፣ ካልተሠራ የማይኖር ከሆነ፣ የመኖር ትርጉሙ ምንድን ነው? የምንኖረው "ለሥራ" ነው ማለት ነው? እንዲያማ ባይሆን ኖሮ ትርፉ ድካም፣ እንዲያው መሮጥ መባከን አይሆንብንም ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ግን ይህን አይደለም፡፡ ሥራ በረከት እንጂ ርግማን ወይም ፍርጃ ወይም ድካም አይደለም፡፡ ሠራተኞች እንድንሆን ያደረገን ውድቀታችን ሳይሆን ፍጥረታችን ነው፡፡ ምክንያቱም የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ሠራተኛ አምላክ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሥራ የተከበረ ተግባር መሆኑን የምናውቀው፣ እግዚአብሔር ራሱ ታታሪ ሠራተኛ ስለሆነ ነው፡፡ ሥራን የፈጠረና ያከበረ አምላክ ካለ፣ እኛም የተፈጠርነው በእርሱ አምሳል ከሆነ፣ እኛም ሥራን ልናከብርና ለሥራም የተለየ ግምት ሊኖረን ይገባል፡፡ ታታሪው ሠራተኛ በየቀኑ ሥራውን ካከናወነ በኋላ የሠራውን ነገር መለስ ብሎ ሲመለከት "ያ መልካም እንደ ሆነ አየ" (ዘፍ 1÷11፡13፡19፡21፡25)፤ በተለይ ደግሞ በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው ሲመለከት "እነሆም እጅግ መልካም ነበረ" (1÷31)፡፡ ከዚያም "እግዚአብሔር...ገነትን ተከለ...ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው" (ዘፍ

[45] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 185-186፡፡
[46] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 186-187፡፡
[47] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 187-188፡፡

2÷8-15)። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ገነትን እንደ ተከለ፣ ሰውን እንደ ፈጠረና ለሰውም ሥራ እንደ ሰጠ እንመለከታለን። ይህም እግዚአብሔር ራሱ ሠራተኛ አምላክ ብቻ ሳይሆን፣ በአምሳሉ ለፈጠረውም ሰው ሥራውን እንዳካፈለ ያሳየናል።

እንግዲህ ሥራ ክቡር የሆነው፣ ከእግዚአብሔር የተነሣ ነው። ሥራ የርግማን ውጤት ሳይሆን የኪነ ፍጥረቱ ውጤት ነው። እንዲህ ሲባል ግን የምንሠራው ለመኖር ነው ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ለመሥራትና ለመፍጠር እንኖራለን። እግዚአብሔር ሠራተኛ ፍጡር አድርጎ ስላበጀን እኛም እንደ እርሱ እንሠራለን፤ እንፈጥራለን። የፈጠራ ክሂሎታችን ከየትም የተገኘ አይደለም፤ ካተመብን አምሳሉ እንጂ።

እዚህ ላይ አንድ በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነገር እንዳለ ለማሳሰብ እንወዳለን። ይኸውም ሥራ ክቡር ተግባር ቢሆንም፣ ዝንተ ዓለማችንን በሥራ ተጠምደን ትልቁን ነገር እንድንረሳ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። አንድ ወዳጄ ከአንድ አዛውንት የሰማሁት ተረት ነው ብሎ ያጫወተኝ ቁም ነገር አሁን ላነሣነው ርእሰ ጉዳይ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፦ "ዐሣማ በዕድሜዋ ዘመን ሁሉ ሰማይን የምታየው አንድ ቀን ብቻ ነው አሉ፤ ልትታረድ ገልበጥ ስትደረግ። ከእርሷ በላይ ሌላ የተለየ ዓለም እንዳለ የምታስተውለው፣ በዚያች ቢላዋው ካንገቷ በሚገናኝበት ቅጽበት ነው። ታዲያ ምን ያደርጋል፣ ከቶ መመለስ ወደማትችልበት ዓለም ስለ ሄደች ያስተዋለችውን አዲስ ዓለም ለማየት ጊዜው አልፎባታል"። ዐሣማዋ ዘመኗን ሁሉ ያሳለፈችው ምሳር ምሳሯን ስትል ነው። ለምግቧ እንጂ በዙሪያዋ ስላለው ዓለም ደንታ አልነበራትም። ወደ ታች ብቻ እንጂ ወደ ላይ ሌላ ዓለም ያለ አልመሰላትም። ራስ ራሷን ስታይ ሰማዩ ተከደነ። ሰዎች የተፈጠሩት ወደ ታች እያዩ ወደ ታች እንዲቀሩ አይደለም። ወደ ታችም ወደ ላይም እንዲያዩና የምድር ሥራቸውን ለሰማዩ አምላካቸው ክብር እንዲያውሉት ነው። ኑሮአቸውንም ከፈጣሪያቸው ጋር እንዲያዛምዱት ነው።

ከሥነ ፍጥረት ታሪክ እንደምንረዳው፣ የፍጥረት ግብ ፈጣሪን ማሰብ ነው። ማለትም ሁለመናችንን ለሥራ ሰጥተን ፈጣሪያችንን እንድንረሳ አይደለም። መሥራት እንዳለ ሁሉ ከፈጣሪም ጋር መራከብ አለ። ሰውን ሰው ያሰኘው ማርክሳውያኑ እንደሚሉት ሥራው ሳይሆን፣ አምልኮው ነው። እውነተኛ ደስታና እርካታ ብዙ በሠራን ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከአምላካችንና ከፈጣሪያችን ጋር ብዙ በተራከብን (ኅብረት ባደረግን) ጊዜ ነው። ምክንያቱም የሕይወት ግብ እግዚአብሔር እንጂ ሥራ አይደለም። ሥራ የራሱ የሆነ አምላካዊ ግብ ቢኖረውም፣ መላ ነገራችንን ግን ከእግዚአብሔር ሊነጥለው አይገባም። ሰባኪው እንዳለው "ሁሉ ነገር ከንቱ ነው፤ እንዲያውም የከንቱ ከንቱ ነው" (መክብብ 1÷1)። ለዚህ ሰባኪ "ከፀሓይ በታች" (ማለትም ያለ እግዚአብሔር) ሁሉም ነገር ከንቱ ነው። ለእኛም ሆነ ለሥራችን ትርጉም የሚሰጠው እግዚአብሔር ነውና። ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ተርጉም የላትምና።

## 5. ሥራና ዕረፍት

የሥነ ፍጥረት ታሪክ ሥራን ከዕረፍት እንዳናፋታ ወይም እንዳ ናለያይ ያስጠነቅቀናል። ሥራ በእግዚአብሔር የተፈጠርንበትን ዐላማ እውን ሲያደርግ፣ ዕረፍት ደግሞ በእግዚአብሔር ሥራ ደስ እንድንሰኝ ያደርጋል። በዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን ሥራ ማድነቅ የሚችለው ሰው ብቻ ነው። ሥራ አመላካዊ በረከት እንደሆነ ሁሉ፣ ዕረፍትም አምላካዊ በረከት ነው። የሚሠሩ ሰዎች ማረፍ አለባቸው። ምክንያቱም የመጀመሪያው ሠራተኛ፣ እርሱ ራሱ ከሥራው ዐርፎአል። "እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ።

እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና" (ዘፍ 2÷2-3)። እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ለሰዎች የሰጠው ፍቅሩን ለመግለጽ ነው። ይህ ዓለም ለእርሱ ውድ ዓለም ነው። እርሱ ለዚህ ዓለም ያስባል፤ ለዓለሙም መልካም የሆነውን ያደርጋል[48]።

እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን ከሥራችን እንድናርፍ ነው። እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ያረፈው ስለ ደከመው አይደለም። ሥራውን ስለ ጨረሰ ነው። የእኛም ዕረፍት ይህን ምሳሌ መከተል አለበት። የምናርፈው ሥራችንን ስለጨረስን ነው፤ አሁን የሠራነውን መለስ ብለን የምንመለከትበትና በሠራነውም ደስ የምንሰኝበት ነው። እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ያሳለፈው በድካም ሳይሆን በመንፈስ እርካታ ነው[49]። ደግሞም እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን በእርሱ እንድናርፍ ነው። በእርሱ መታመንን የምንማረው በእርሱ ስናርፍ ነው። እስራኤልም በሰባተኛው ቀን እንድታርፍ የታዘዘችው በዚህ አምላክ መታመንን እንድትማር ነው። ያኔም ሆነ አሁን ሕይወት በእኛ ጥረት የተመሠረተች አይደለችም። እኛ ካልሠራን ሕይወት ብን ብላ አትጠፋም። ምክንያቱም ሕይወት ስጦታ ናት። በሚያሳርፈው ታምኖ ማረፍ ተገቢ ነው። እርሱ ታማኝ ነውና[50]። እንዲሁም እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን ሁላችንም በእርሱ ፊት እኩል መሆናችንን ሊያሳየን ነው። ሰንበት ለሰው ልጆች ሁሉ (ለሀብታሙም ሆነ ለደኻውም) የተሰጠ በረከት ነው።

እግዚአብሔር የመጀመሪያው ሠራተኛ ነው። ሥራውም ሙሉ ነው። ከፍቅሩ የተነሣ ዓለምንና ሰውን ፈጠረ። ከፍቅሩም የተነሣ ሰንበትን ለሰው ልጆች ሰጠ። ሰንበት ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያስተምረን አንድ ብርቱ ነገር አለው። ይኸውም እግዚአብሔር የሚያርፍና የሚያሳርፍ አምላክ ነው። እንደ ባቢሎናውያን አማልክት ዘመኑን ሳምንቱንና ቀኑን ሁሉ በሥጋት አያሳልፍም። የሰው ልጆች ጉድ ይሠሩኝ ይሆን ብሎ ሲጨነቅ አይውልም። በሰንበት ቀን ስናርፍ እግዚአብሔርን አንተ ጌታ ነህ ማለትም መጋቤ ኩሉ ነህ በማለት እያወጅን ነው[51]። በሰንበት ቀን ከሥራችን ሁሉ ስናርፍ ሕይወታችን በእግዚአ ብሔር እጅ መሆኗን እያረጋገጥን ነው። ከሥራችን እናርፋለን፤ ምክንያቱም ተስፋችን ሥራችን ሳይሆን እግዚአብሔር ነው[52]። እንግዲህ በሰንበት ቀን አለማረፍ በሥርዐቱ ፈጣሪ ማለትም ሥርዐቱን ባቆመው አለማረፍ ነው። ደግሞም ሰንበትን አለማክበር የሥርዐቱን ፈጣሪ አለማክበር ነው። ለሕይታችን ትርጒም የሚሰጠው ሥራ ሳይሆን እግዚአብሔር ነውና[53]።

## 6. ሥራ ከመስቀሉ፣ ከኅብረተሰቡና ከአዲሱ ፍጥረት አንጻር

እስከ አሁን ድረስ ሥራ ምን እንደ ሆነና ለሥራም ምሳሌያችን ማን እንደ ሆነ ስንመለከት ቈይተናል። አሁን የሚቀረን ሥራን ከሦስት መሠረታዊ መርሖች አንጻር ማጤን ነው - ከመስቀሉ፣ ከኅብረተሰቡና ከአዲሱ ፍጥረት።

---

48 John Goldingay and Robert Innes, *God at Work* (Nottingham: Grove Books Limited, 1994), 10.

49 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 11።

50 Walter Brueggemann, *Genesis*, Interpretation (Georgia: John Knox Press, 1982), 33-35.

51 Bruce K.Waltke, *Genesis: A Commentary* (Grand Rapids: Zondervan, 2001), 67-68; 71-73.

52 J.R.Wilson, *Gospel Virtues: Practicing Faith, Hope and Love in Uncertain Times* (Downers Grove: Inter Varsity, 1998), 129.

53 A.J.Heschel, *The Sabbath: Its Meaning for Modern Man* (New York: Farrar, Straus & Giroux, 1986), 3.

### 6.1. ሥራ ከመስቀሉ አንጻር

**መስቀሉ በብዙ ረገድ ምሳሌያችን ነው፡፡ ከሁሉ በፊት ግን የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር በተጨባጭ ያየንበት ሁነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደን ለማወቅ ወዴትም መሄድ አያስፈልገንም፤ ወደ መስቀሉ ከሄድን በዚያ ታላቅ ፍቅሩን እናገኛለን፡፡ ግን ደግሞ መስቀሉ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ የምናይበትም ሁነት ነው፡፡ ስለ መስቀሉ መናገር ለዓለም ሞኝነት ነው፡፡ ምክንያቱም የውርደት ምልክት ነው፡፡ የከበረው ወዳልከበረው አይወርድም፡፡ እግዚአብሔር ግን በዓለም ዘንድ የተናቀውን መንገድ መረጠ፡፡ በዓለምም ፊት እንደ ምናምንቴ የሚቈጠረውን ጎዳና ተጓዘ፡፡ በተናቀ ነገር መሥራት የእግዚአብሔር ፖሊሲ ነው[54]፡፡ አሁን ነገሮች ሁሉ መታየት ያለባቸው ከመስቀሉ አንጻር ነው፡፡ ምክንያቱም መስቀሉ ለምንም ነገር መነሻችን ሆኖአል[55]፡፡**

**ስለ ምንም ነገር ለመናገር ከፈለግን ከመስቀሉ መጀመር አለብን፡፡ ስለ ጥበብ፣ ኀይል፣ ሥራ፣ ዕረፍት፣ ወዘተ እንናገር ካልን ከመስቀሉ ጋር እያገናዘብን መናገር አለብን፡፡ ውድቀት መንገዱን ሰወረብን፡፡ ምድርን እንድንከባከብ ዐደራ ተሰጥቶን ነበር፡፡ እኛ ግን ምድርን በዘበዝናት፡፡ ሠራተኛ ሕዝብ እንድንሆን ተጠርተን ነበር፡፡ እኛ ግን ሐኬተኞች ሆንን፡፡ ይሁን እንጂ መስቀሉ አዲስ መንገድ ይሆነን ዘንድ ተሰጠን[56]፡፡ ከዚህ በፊት የኖርነውን የስንፍናና የብዝበዛ ሕይወት እርግፍ አድርገን እንድንተው ምሳሌ አኖረልን፡፡ ይህን ሁሉ የለወጠው መስቀሉ ነው፡፡ የዓለም መንገድና መርሕ በመስቀሉ ተቀልብሷል[57]፡፡**

### 6.2. ሥራ ከኅብረተሰቡ አንጻር

**ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲያውጅ ዕቅዱ፣ አዲስ ኅብረተሰብ ለመመሥረት ነው፡፡ ይህች አዲስ ኅብረተሰብ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥቱን መራሔ ጽድቅ በመልበስ አዲስና የተዋጀች ኅብረተሰብ ሆናለች[58]፡፡ እግዚአብሔር የዚህን ዓለም ብልሹ ሥርዐት ለመለወጥ የፈለገው፣ በዚህች ኅብረተሰብ አማካይነት ነው፡፡ የምትለውጠውም አዲሱን ሥርዐት በአሮጌው ሥርዐት መካከል በመግለጥ ነው፡፡ አሮጌው ሥርዐት ዐመፀኛነትንና ሐኬተኛነትን መርሑ አድርጓል፡፡ አዲሱ ሥርዐት ደግሞ ንቁነትንና ትጉህነትን መርሑ አድርጓል[59]፡፡ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው መስቀሉ አዲስ መንገድና አዲስ ሕይወት ነው፡፡ በመሆኑም አዲሱ**

---

[54] Tom Sine, *The Mustard Seed Conspiracy* (Word, 1981) ገጽ 11-12 ፡፡ እንዲሁም Joel B. Green and Mark D. Baker, *Recovering the Scandal of the Cross: Atonement in the New Testament and Contemporary Contexts* (Downers Grove: InterVarcity Press, 2000) ገጽ 47-52 ይመለከቷል፡፡

[55] Richard B. Hays, *First Corinthians*, Interpretation (Louisville: John Knox Press, 1997), 26-31.

[56] Alexandra R. Brown, *The Cross and Human Transformation: Paul's Apocaliptic Word in 1 Corinthians* (Minneapolis: Fortress, !995), 12.

[57] Anthony C. Thiselton, *The First Epistle to the Corinthians*, NIGTC (Grand Rapids: Eerdmans, 2000), 169.

[58] John Stott, *New Issues Facing Christians Today*, 85.

[59] John Howard Yoder, *The Politics of Jesus* (Grand Rapids: Eerdmans, 1972) ገጽ 111 እና 157፡፡

ኅብረተሰብ እንዲኖር የተጠራው በመንግሥቱ መራሕያን መሠረት ነው፡፡ የመንግሥቱ መራሕያን የምድር ጨውና የዓለም ብርሃን እንድንሆን ይጋብዘናል (ማቴ 5÷13-16)፡፡

ይህ ዓለም በጨለማ የተወረሰ ዓለም ነው፡፡ ደግሞም እየሞተና እየበሰበሰ ያለ ዓለም ነው፡፡ ምግባራዊ እሴቶች ከምን ጊዜውም በላይ እየወደቁ ናቸው፡፡ ሕዝቦች በአስተሳሰባቸው ከምን ጊዜውም በላይ እየዘቀጡ ናቸው፡፡ ዐመፀኛነት፣ ጉቦኛነት፣ ሐኬተኛነት፣ ራስ ወዳድነት ከምን ጊዜውም በላይ እየናኘ ነው፡፡ የሰው ሕይወት የተናቀበት፣ የራስ ጥቅም የነገሠበት ዓለም ነው፡፡ ጥፋቱ የማን ነው? የሚወቀሰውስ ማን ነው? ጌታ ኢየሱስ፣ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ሲለን፣ ትልቅ ኀላፊነት እንዳለብን እያሳሰበን ነው፡፡ ምሽቱ እየበረታ ሲመጣ ቤቱ ቢጨልም፣ ቤቱን መውቀስ አንችልም፡፡ ምክንያቱም ፀሓይ ስትጠልቅ ቤቱ ይጨልማል፡፡ ጥያቄው "ብርሃኑ የት አለ?" የሚለው ነው፡፡ ልክ እንዲሁ ሥጋ ሲበሰብስ ለምግብነት ሊውል አይችልም፤ ሥጋውን መውቀስ አንችልም፡፡ ምክንያቱም ባክቴሪያዎች እንዲራቡ ከተፈቀደላቸው ሥጋውን ያበሰብሱታል፡፡ ጥያቄው "ጨው የት አለ?" የሚል ነው፡፡ ይህ ዓለም በራሱ መንገድ እንዲሄድ ከተተወ ይነቅዛል፤ ይዘቅጣል፤ ዐይነ ተኩላውም ይጠፋል፡፡ በኀጢአት የወደቀ ዓለም በመሆኑ ይበልጥ እንዳይዘቅጥ ካልተጠበቀ ክፋት ይናኛል፤ ዐመፅ ይሰፍናል፤ ራስ ወዳድነትም ይነግሣል፡፡ ጥያቄው "ቤተ ክርስቲያን የት አለች?" የሚል ይሆናል፡፡ በምድራችን ሐኬተኛነት ቢሰፍን ተጠያቂው እኛ ነን፡፡

## 6.3. ሥራ ከአዲሱ ፍጥረት አንጻር

ክርስቲያኖች በንቃት የሚጠበቁ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የዓለም ሁሉ ዐይን በእነርሱ ላይ ነው፡፡ ሕይወታችን በየዕለቱ ይመዘናል፡፡ በቤትም ሆነ በውጭ ሰው ሁሉ ትኩር ብሎ ይመለከተናል፡፡ በጌታ የተጠራነው የዓለምን ሥርዐት እንድንለውጥ፣ የዓለምን ሥርዐት እንድንቀለብስ ነው፡፡ የተለየ ሕይወት በመኖር ብልሹውን ሥርዐት መገዳገድ ይኖርብናል፡፡ ብርሃንና ጨው መሆን ማለት የተለየ ሕይወት መኖር ማለት ነው፡፡ ያን የተለየ ሕይወት ኢየሱስ በአንድ ቃል ሲያጠቃልለው እንዲህ ይለናል፣ "እናንተ ግን እንደ እነርሱ አትሁኑ" (ማቴ 6÷8)፡፡ የተጠራነው ለላቀ ሕይወት እንደ ሆነ የሚገልጽ ምክር ነው፡፡

ይህን ከተነሳንበት አርእስት ጋር ስናያይዘው፣ ብዙ ልናስብባቸው የሚገቡ ነገሮች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ አንደኛው ሥራችን የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ መገንዘብ አለብን፡፡ ሥራን በተመለከተ የሚነገሩትን አሉታዊ ነገሮች (ሥራ ፍዳ ነው፤ ሥራ ጣጣ ነው) ለማሸነፍ የምንችለው በሥራና በአምልኮ/ጥሪ መካከል ያለውን ዝምድና መረዳት ስንችል ነው፡፡ አብርሃም ማስሎ የተባለ ሰው ለሰው ልጆች የሚያስፈልጉና እጅግ ወሳኝ ናቸው የሚላቸውን መሠረታዊ ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አብርሃም በዝርዝሩ ውስጥ ያላካተተው አንድ ዐቢይ ነገር አለ-አምልኮ፡፡ ሥራ አምልኮ ነው ሲባል በምንሠራው ማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን መመልከት አለብን ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰጠንን ዐደራ ስንፈጽም እግዚአብሔር እናከብራለን፡፡ አምልኮአችን ሙሉ የሚሆነው የሥራችንን ፍሬ መልሰን ለእርሱ ስንሰጥ ነው፡፡ ከእኛ የሆነ ምንም ነገር ከሌለ፣ ለእኛ ክብር የሚውል ምንም ነገር አይኖርም[60]፡፡

[60] Graham Dow, *A Christian Understanding of Daily Work* (Cambridge: Grove Books Limited, 2000), 19-20.

ሁለተኛው ሥራችን ልቀት የሚታይበት መሆን አለበት። ክርስቲያኖች ለላቀ ሥራ ተጠርተዋል። በነገር ሁሉ ልቀት ግባችን ሊሆን ይገባል። ውሽልሽሎች ልንሆን አይገባም፤ ማለትም የግብር ውጣ ሥራ በእኛ ዘንድ ሊታይ አይገባም። ምርጥ ማለትም የተመሰገነና የተከበረ ሥራ ለመሥራት መጣር አለብን። የተሰጠንን ሥራ አሳምሮ በመሥራት ልንታወቅ እንጂ ልንወቀስ አይገባም።

ሦስተኛው ከቤት ጀምሮ እስከ ውጭ ድረስ በማንኛውም ሥራ መሳተፍ አለብን። የግልና የቤት ንጽሕናችንን መጠበቅ አንዱ ሥራ ነው። የግቢያችንንና የአካባቢያችንን ጽዳት መጠበቅ ሌላው ሥራ ነው። ጽዳትን መጠበቅ እኮ ትልቅ ሥራ ነው። ቈሻሻ በየመንገዱ መጣል፣ ሽንት በየጕዳናው መሽናት፣ የቤት ጥራጊ በየቦዩ መድፋት ነውር፣ ከዚያም ዐልፎ በደል እንደ ሆነ መገንዘብ አለብን።

በመጨረሻም  ዕረፍት ተገቢ እንደ ሆነ መገንዘብ አለብን። ሰንበት እናርፍበት ዘንድ ለሰዎች ሁሉ ተሰጠ። በዕለተ ሰንብት ሰዎች ሁሉ ከሥራቸው መተንፈስና በሥራቸው መደሰት አለባቸው። እርግጥ ከውድቀት በኋላ የሰንበት እውነተኛው ትርጒሙ ጠ ፍቶብናል። በእግዚአብሔር ታምኖ ነገርን ለእርሱ መተው አደጋ ያለው ይመስለናል። ወይም የምናጣው ነገር ያለ ይመስለናል። ሰዎችን እንደ ባርያ መግዛት የዚህ ዓለም እኩይ ሥርዐት ነው። ለክርስቲያኖች ግን ይህ ፍጹም ውጉዝ ነው። መልካምነት ከእኛ ሊታጣ አይገባም። ለሰዎች ሰብእና ልንጨነቅ ለዕረፍታቸውም ልናስብ ይገባል።

እግዚአብሔር የፈጠረን ከእርሱ ጋር አብረን እንድንሠራ ነው። እርሱ የሥራ ጌታና የሥራ ምሳሌ ነው። ማለትም ሥራን የፈጠረና የሥራም ምሳሌ እርሱ ነው። እንግዲህ የሰዎች ሥራ ትርጒም የሚያገኘው ከእርሱ የተነሣ ነው። ሥራችን ምንም ይሁን ምን ከእርሱ ተነጥሎ መታየት የለበትም። እኛ የምንሠራው ማንኛውም ሥራ የእርሱ ሥራ ነጸብራቅ ነው። የዕለቱንና የቀኑን ሥራችን እግዚአብሔር ሥራ ነው[61]። በዚህ ዓለም "ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና" (1ቆሮ 3÷9)።

[61] Graham Dow, *A Christian Understanding of Daily Work* (Cambridge: Grove Books Limited, 2000), 7.